አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3562 | ቅዳሜ የካቲት 21 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# እየጎለበተ የመጣው ወዳጅነት

**“በሁለቱ ሀገራት የወል ፍላጎት ላይ ተመስርተን ትብብራችንን የምናሳድግባቸውን መንገዶች ተመልክተናል”**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**“ትብብራችን በቀጣናው የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የሚቀጥል ይሆናል”**

**የእስራኤል ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ**

**በመለሰ ተሰጋ**

ኢትዮጵያንና እስራኤልን በታሪክ፣ በእምነትና ባህል ያቆራኘችው ንግስት ሳባ እንደሆነች የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ንግስት ሳባ ወደ እስራኤል አቅንታ ከጠቢቡ ሰለሞን ቀዳማዊ ምኒልክን መውለዷን ከዚያም ታቦተ ፅዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን ተከትሎ በሀገራቱ መካከል ያለው የባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና መሰል ግንኙነቶች ከፍ ማለታቸውም እንዲሁ፡፡

በሌላ በኩልም መፅሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳን) ከዓለም ቋንቋዎች ሁሉ ቀድሞ ከእብራይስጥ ቋንቋ የተተረጎመው ወደ ግዕዝ ነው፡፡ ይህንንም እውነት የዐባይን መነሻ ለማየት በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የተጓዘው ስኮትላንዳዊው ጀምስ ብሩስ፣ “በግዕዝ እና በእብራይስጥ መካከል ያለው መመሳሰል የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ለማለት

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ ኢትዮጵያን እና እስራኤልን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል

## የሀገራዊ ትርክት መሰረቶች

6



ፎቶ- ከፋይል

በመዲናዋ ለወል ትርክት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ስራዎች መካከል አንዱ የሆነው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ከፊል ገጽታ

## የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አዲስ ስጦታ

11



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ’ቡቤ’ የተሰኘ ድራማ ለመጀመር የስራ ስምምነት ተፈራርሟል

## በሮም የተደገመው የዓድዋ ድል

20



ፎቶ- ከገፀ ድር

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1960 በሮም ኦሎምፒክ በባዶ እግሩ ሮጦ ዓለምን ያስደመመው ሻምበል አበበ ቢቂላ

# የአዲስ አበባ የሰላም ተምሳሌትነት

**“ሰላምን አስተማማኝና ዘላቂ ለማድረግ ሕዝብን የሰላም ባለቤት ማድረግ ወሳኝ ነው”**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በ8ኛው ሀገር አቀፍ የሰላምና ፀጥታ ምክክር መድረክ ላይ ንግግር አድርገዋል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው። ከተሞችን ለሥራ፣ ለንግድና ቱሪዝም እንዲሁም ለኑሮ ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ወሳኝ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ሰላም ነው። ዜጎች በሰላም ወጥተው መግባት፣ ያለገደብ ተንቀሳቅሰው መሥራት የሚችሉበትን ሁኔታ የፈጠሩ፣ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ የቻሉ፣ ዝቅተኛ የወንጀል ምጣኔ ያለባቸው ከተሞች ለኑሮ ተመራጭ ናቸው።

ወደ ገጽ 5 ዞሯል






# ዓድዋ፤ የኢትዮጵያውያን መልክ እና የከፍታ ልክ

- **ትውልዱ ውስጣዊ አንድነት ማጠናከርን ከዓድዋ መማር እንደሚገባው ተጠቁሟል**


**በመለሰ ተሰጋ**

ኢትዮጵያዊነት ቅኔ ነው፤ ሰምና ወርቅ ነው። ቆላ፣ ደጋ፣ ወይናደጋ እና በረሃውን፣ ጥቁር፣ ቀይ፣ ጠይምና የቀይ ዳማውን እንደ ቡሄ ጅራፍ በወጉ ገምዶ፣ እንደ ፊደልና ቃል አዋህዶ ግሩም ትርጓሜን የያዘ ድንቅ ማንነት ነው፡፡ ለዚህ ውድ ስጦታ ኢትዮጵያውያን በየዘመናቱ በአንድነት ተምመው ዋጋ ከፍለውበታል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## አዲስ አበባ በልማት ያሳየችው ለውጥ የዚህ ዘመን ዳግማዊ የዓድዋ ድል ነው!

የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን የነፃነት፣ የአንድነትና የማንነት ማህተም ነው። መላው ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር በመተባበር ያስመዘገቡት ታላቅ ድል ነው። ይህ ድል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ከማስጠበቅም ባለፈ፣ ለመላው ጥቁር ሕዝቦችና ለአፍሪካውያን የነፃነት ተጋድሎ ብርሃን የሆነ፣ ቅኝ ግዛትን መስበር እንደሚቻል በተግባር ያሳየ ታሪካዊ ክስተት ነው።

በታሪክ አጋጣሚ የዓድዋ ድል የተበሰረባት አዲስ አበባ፣ ዛሬም የዚያኑ ያህል የገዘፈ ኃላፊነት አለባት። ከተማዋ የአፍሪካ መዲናና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ እንደመሆኗ፣ ይህንን ከፍታ የሚመጥን ገጽታ እንዲኖራት ግድ ይላል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተከናወኑት አስደናቂ የልማት ሥራዎች፣ ከተማዋን ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋገሩና የዓድዋን ድል መንፈስ በልማት የደገሙ ናቸው። በአጭር ጊዜ ውስጥ የተመዘገቡት ውጤቶች ኢትዮጵያውያን ከተባበሩና ካቀዱ የማይቻል ነገር እንደሌለ በድጋሚ ያረጋገጡ ሆነዋል።

ከእነዚህ የልማት ሥራዎች መካከል የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የከተማዋን ውበት ከመጠበቅ ባለፈ፣ ነዋሪዎች ምቹና ዘመናዊ የኑሮ ሁኔታ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ትልቅ ለውጥ አምጥተዋል። የወንዝ ዳርቻዎች ከቆሻሻ መጣያነት ወደ መዝናኛ እና የቱሪስት መስህብነት መቀየራቸው፣ እንዲሁም የከተማዋን መሠረተ ልማት ያዘመኑት የኮሪደር ሥራዎች አዲስ አበባን እንደ ስሟ 'አዲስ' አድርገዋታል።

የኮሪደር ልማቱን ተከትሎ መንገዶች ሰፍተዋል፤ ምቹና ውብ የእግረኛ መንገዶች ተሰርተዋል፤ የመንገድ ዳርቻዎች በተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችና በውብ መብራቶች አሸብርቀዋል፡፡ በገበታ ለሸገር መርሃ ግብርም እንደ እንጦጦ እና አንድነት ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ የመሳሰሉ ልማቶች ተከናውነዋል፡፡ በተጨማሪም የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ ሳይንስ ሙዚየም፣ አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከልን የመሳሰሉ ድንቅ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ይህ ፈጣንና ጥራት ያለው የልማት እንቅስቃሴ፣ የከተማዋን ዲፕሎማሲያዊ ክብደት የሚመጥን ተግባር ነው። በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወራት ውስጥ ከተማዋ ከ150 በላይ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን እንድታካሂድ ትልቅ አቅም ፈጥሯል፡፡

ይህ በአጭር ጊዜ የታየ ለውጥ 'የዘመኑ የዓድዋ ድል' ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ጥንካሬውና ትብብሩ ልክ እንደ አባቶቻችን በጦር ግንባር ሳይሆን፣ ዛሬ በልማትና በብልጽግና ግንባር እየተገለጠ ይገኛል። የኮሪደር ልማቱ ስኬት የሚያሳየው፣ በትክክለኛ አመራርና በሕዝብ ተሳትፎ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ነው። ይህ ስኬት ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን "እኛም እንችላለን" የሚል አዲስ ተስፋና ትምህርት የሚሰጥ ድንቅ ተሞክሮ ሆኖ ተመዝግቧል።

የዚህ ዘመን ትውልድ ካለፈው ታሪክ ወርቃማ ገጾችን እየቀሰመ፣ ለነገዋ ኢትዮጵያ የማይደበዝዝ አሻራ ማኖር ይኖርበታል። አዲስ አበባን የማዘመንና የመገንባት ጉዞ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትም ለዚሁ ነው። የዛሬው ትውልድ በልማት የሚያስመዘግበው ውጤት፣ ልክ እንደ ዓድዋ ድል ለዘመናት ሲታወስ የሚኖር ኩራት ይሆናል። በመሆኑም፣ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን በባለቤትነት ስሜት በመጠበቅና አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን በማከል፣ ኢትዮጵያንና መዲናዋን ወደ ላቀ የብልጽግና ማማ ላይ የማውጣት ታሪካዊ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## የአገልግሎቱ ሁለት ገጽታዎች

**በቸርነት ዋለልኝ ከአራብሳ**

አንድ የቅርብ ወዳጄ አብዛኛውን ጊዜ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት አግኝቶ ሲመለስ ፊቱ በደስታ በርቶ አይቼው አላውቅም። "ዛሬስ እንዴት ነበር?" ብዬ ስጠይቀው፣ የሚሰጠኝ ምላሽ "አሁንም ያው ነው፤ ነገ ና ተባልኩ" ወይም "የፊታቸው መኮሳተር አገልግሎቱን እንድጠላው አደረገኝ" የሚል ነው። የዚህ ወዳጄ ስሜት የብዙዎቻችን የዕለት ተዕለት ገጠመኝ መሆኑ ደግሞ ነገሩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል።

በአገልግሎት ሰጪ እና ተቀባይ መካከል ያለው ግንኙነት የአንድን ሀገር ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚያቀላጥፍ ትልቅ ሞተር ነው። በዚህ አገልግሎት የመስጠትና ማግኘት ሂደት ውስጥ የደንበኞች አገልግሎት እርካታ የሚል ርዕሰ ጉዳይ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ መታረም ያለባቸው ስራዎች ሲኖሩ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አቅጣጫ ማመላከት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ይበል የሚያሰኙ ተግባራት ሲገጥሙንም ማመስገን ይገባል ባይ ነኝ፡፡ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም። በተለይ በመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚታየው ትልቁ ክፍተት አገልግሎትን እንደ "ችሮታ" የማየት አባዜ ነው። አንድ ተገልጋይ መብቱን ለማግኘት ሲመጣ፣ በአግባቡ መስተናገድ አለበት፡፡ ተገልጋይ መሆኑ ቀርቶ "ነገረኛ" ወይም "አስቸጋሪ" ተደርጎ የሚታይበት አጋጣሚ ብዙ ነው።

በተቋማት አገልግሎት ላይ ከቢሮክራሲው ጀምሮ እስከ ግለሰባዊ የባህሪ መበላሸት ድረስ ያሉት ችግሮች መፍትሄ ሊበጅላቸው ይገባል። ተቋማት የተገልጋይ እርካታን እንደ ስኬት መለኪያ ሊጠቀሙበት፣ ሰራተኞችም ተገልጋዩን እንደ ራሳቸው ወዳጅና ቤተሰብ የማየት ስነ-ልቦና ሊያዳብሩ ይገባል። ተገልጋዩ መስፈርቱን እስካሟላ ድረስ መስተናገዱ መብቱ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ይህ ሲባል ግን ሁሉም ነገር ጨለማ ነው ማለት አይደለም። አልፎ አልፎ "ይበል" የሚያሰኙ፣ ስራቸውን በቅንነትና በፈገግታ የሚያከናውኑ፣ "ዛሬ ለምን መጣህ?" ሳይሆን "ምን ልርዳህ?" የሚሉ ባለሙያዎች መኖራቸው እሙን ነው፡፡

ከላይ ከመነሻዬ የጠቀስኩት የቅርብ ወዳጄ ይህንኑ እርካታዉን ለማወቅ አፍታም አልወሰደብኝም፡፡ የሄደበት ጉዳይ እንደተሳካለት ከፊቱ ፈገግታ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ የዚህ የእርካታ ምንጭ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመንና ብልሹ አሠራሮችን ለማስቀረት የተቋቋመው አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተቋማት ሊበራከቱ ይገባል ባይ ነኝ።

እንደ ሀገር ለማደግና የሰለጠነ ማህበረሰብ ለመገንባት፣ አገልግሎት ሰጪው "ዛሬ የኔ ተራ ነው" በሚል ቅንነት፣ ተገልጋዩ ደግሞ "መልካም ስራን ማበረታታት አለብኝ" በሚል የዜግነት ግዴታ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል ብዬ አስባለሁ።

ተገልጋዩ "ዛሬማ በጣም ደስ የሚል መስተንግዶ ነበረ" ብሎ የሚናገርበት ቀን ቀጣይነት እንዲኖረው፣ ሁላችንም በቆምንበት መስክ የአገልግሎት ባህላችንን እንፈትሽ። ትችታችን ጠንካራ እንደሆነው ሁሉ፣ ምስጋናችንም ድምፅ ይኑረው።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ሄለን ጥላሁን
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# እየጎለበተ ... ከገጽ 1 የዞረ

ይከብዳል” ሲል በማስታወሻው አስፍሯል፡፡

ይሁን እንጂ የሀገራቱ ግንኙነት በዘመናዊ መልኩ የጀመረው እ.ኤ.አ 1956 በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት እንደሆነ ድርሳናት ዋቢ ይሆናሉ፤ ሀገራቱ በልዩ ልዩ ልማቶች እና የወቅቱን ቀጣናዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ትስስርም በየዘመናቱ እያደረጉ መቀጠላቸውን የታሪክና ስነ ልቦና ባለሙያው አቶ ማህደር ሳልህ ይናገራሉ፡፡

የሁለቱ ሀገራት ዘመናትን የተሻገረው ግንኙነት አሁን ላይ በተለያዩ መስኮች የተጠናከረ ሆኖ ይገኛል። የሀገራቱ ግንኙነት ግን በየዘመኑ በነበሩ መንግስታት ፖለቲካ ርዕዮት ምክንያት ከፍም ዝቅም እያለ ጥንካሬውን አስጠብቆ የቀጠለ መሆኑንም የታሪክ ባለሙያው ገልጸዋል፡፡

በተለይም ዴር ሱልጣንን ጨምሮ በኢየሩሳሌም የሚገኙ የኢትዮጵያ ገዳማት የሁለቱን ሀገራት ባህላዊ ትስስር በፅኑ መሰረት ላይ ገንብተዋል፡፡ ይህ ታሪካዊና ባህላዊ ትስስር ከእስራኤል ሀገረ መንግስት ዳግም መመስረትን ተከትሎም እየጎመራ ስለምመጣቱም የታሪክ ባለሙያው አብራርተዋል፡፡

ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አማረ ከበደ እንደሚሉት ደግሞ የዘመናዊ የኢትዮ-እስራኤል ዲፕሎማሲያዊ ወዳጅነት የተወጠነው በአውሮፓውያኑ ዘመን ቀመር በ1956 ነው፡፡ ይህ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመን መንግስት የተጀመረው የሀገራቱ ዘመናዊ ዲፕሎማሲ ስትራቴጂካዊ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ እና የወቅቱን የቀጣናውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በዚሁ ዘመን የነበረው የሀገራቱ ወዳጅነትና ትብብር በተለይ በወታደራዊ እና በልዩ ልዩ ልማታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ቀደም ባሉት ዓመታት የነበረው የሀገራቱ ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ግን የኢትዮጵና የእስራኤል ግንኙነት ወደ ላቀ ስትራቴካዊ አጋርነት እያደገ እንደመጣም ተናግረዋል።

ለአብነትም በ2011 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በእስራኤል ያደረጉትን ይፋዊ ጉብኝት በተምሳሌትነት ያወሱት የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንጃሚን ኔታንያሁ ወሳኝና ታሪካዊ ምክክር አድረገዋልም ብለዋል።

በወቅቱም ሁለቱ ሀገራት ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት ማብራሪያም የሁለትዮሽ ትብብራቸውን ማጎልበት የሚያስችሉ ስምምነቶችን በኢኮኖሚ፣ በግብርና፣ በውሃ፣ በመስኖ፣ በጤና እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም በጸጥታ ዘርፎች ላይ አብሮ ለመስራት መስማማታቸው ይታወሳል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ገነነ ካሳዬ እንደሚሉት ደግሞ የሀገራቱ ግንገኙነት በተለይ በኢኮኖሚው ዘርፍ ትልቅ ስፍራ ያለው ነው፡፡ ለአብነትም



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እና ከፍተኛ አመራሮች የእስራኤሉን ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግን የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሲያስጎበኙ

የእስራኤል ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በዘመናዊ ግብርና እና በሌሎች ዘርፎች ተሰማርተዋል። በማምረቻ ዘርፍ በተለይም በጨርቃጨርቅ እና በኬሚካል ኢንዱስትሪዎች፣ በጤናና ፋርማሲዩቲካል ዘርፍ እንዲሁም በማዕድን ዘርፍ በተለይም በፖታሽ በተለይም በግሪን ሃውስ፣ በግብርና ምርት ማቀነባበሪያ እና መሰል ኢኮኖሚ ዘርፎች ያላቸው ተሳትፎ ከፍ ያለ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ በንግድ ልውውጥ ረገድ ኢትዮጵያ ቡና፣ ሰሊጥና ሌሎች የቅባትና የጥራጥሬ ምርቶችን ወደ እስራኤል በስፋት ትልካለች። በአንጻሩ እስራኤል የላቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ የግብርና ግብዓቶችን (ማዳበሪያና ኬሚካሎች)፣ የሕክምና መሣሪያዎችን እና የደህንነት ቁሳቁሶችን ለኢትዮጵያ እያቀረበች ስለመሆኑም ምጣኔ ሀብት ባለሙያው ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩልም በዓለም አቀፍ ደረጃ በደረቃማ እና በረሃማ አካባቢ ግብርና ስመጥር የሆነችው እስራኤል በዘርፉ የኢትዮጵያ ቀዳሚ የልማት አጋር ናት። በዘመናዊ መስኖ፣ በፍራፍሬ ልማትን መሰረት ያደረጉ በተለይም በእንስሳት እርባታ እና የወተት ምርታማነት አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሀገራቱን ኢኮኖሚያዊ ትስስር እያሳደገች ስለመምጣቷም የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ጠቅሰዋል፡፡

ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አማረ ከበደ ከሰሞኑም የእስራኤል ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ ለይፋዊ ጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው የሁለቱን ሀገራት ለዘመናት የጸና ወዳጅነት ከፍ የሚያደርግና የሀገራቱን ኢኮኖሚያዊና ሁለንተናዊ ግንኙነት የበለጠ የሚያጎለብት ነውም ብለዋል፡፡

ፕሬዝዳንቱ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) እና ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር ብርሃኑ ጻጋዬ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ባሳለፍነው ረቡዕ ፕሬዝዳንት ታዬ

አጽቀሥላሴ በኢትዮጵያ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ያደረጉትን የእስራኤል ፕሬዚዳንት አይዛክ ሄርዞግን በመቀበል በሁለቱ ሀገራት ታሪካዊና ባህላዊ ትስስር ዙሪያ ሰፊ ውይይት ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡

በውይይቱ ወቅት በተለይም የእስራኤል ተወላጅ የሆኑ የቤተ-እስራኤል ማኅበረሰብ አባላት በሁለቱ ሀገራት መካከል እንደ አንድ ሕያው ድልድይ በመሆን ያላቸውን ሚና ይበልጥ ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ትኩረት እንደተሰጠው ፕሬዝዳንት ታዬ አጽቀሥላሴ በማኅበራዊ ትስስር ገጽ ባስተላለፉት መልዕክት ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር ) በበኩላቸው “ዛሬ ወደ ኢትዮጵያ ለይፋዊ ጉብኝት የመጡትን የእስራኤል ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግን ተቀብዬ ፍሬያማ ውይይት አድርገናል” ያሉ ሲሆን፣ “የኢትዮጵያ እና እስራኤልን ግንኙነት በማጤን በወል ፍላጎታችን ላይ ተመስርተን ትብብራችንን የምናሳድግባቸውን መንገዶች ተመልክተናልም” ሲሉ አክለዋል፡፡

የእስራኤሉ ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ በበኩላቸው፣ “በዛሬው ዕለት ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር እጅግ ድንቅ የሆነ ቆይታ አድርጌለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላደረጉልን ደማቅ አቀባበል ምስጋናዬን አቀርባለሁ” ብለው፣ በእስራኤል እና ኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት ትልቅ አቅም ያለው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

“የሁለትዮሽ ግንኙነታችንን ለማጠናከር በኢኖቬሽን፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በግብርና፣ በምግብ ዋስትና፣ በውሃና ኢነርጂ ዘርፎች እንዲሁም ቀጠናዊ ትብብርን ማሳደግን አስመልክቶ ሁለቱን ህዝቦች ተጠቃሚ በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ ፍሬያማ ውይይት አድርገናል” ብለዋል ፕሬዝዳንቱ፡፡

አክለውም፣ “እስራኤል በመላው አፍሪካ ከሚገኙ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር የምታደርገውን ጥረት ገለጻ አድርጌለሁ፡፡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ አህጉር ከሚገኙ ሀገሮች ወሳኝና የእስራኤል ቁልፍ አጋር ሆና ለአስርት ዓመታት የቆየች ሀገር ናት፡፡ ትብብራችን በቀጣናው ዙሪያ ሰላምን፣ አንድነትን እና የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የሚቀጥል ይሆናል” ብለዋል፡፡

የእስራኤሉ ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ በኢትዮጵያ ቆይታቸው የዓድዋ ድል መታሰቢያን ጉብኝተዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክት “ዛሬ ማለዳ ለእስራኤል ፕሬዝዳንት ክቡር አይዛክ ሄርዞግ የመላው ጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነውን የዓድዋ ድል መታሰቢያን እና ለሀገር ሉአላዊነት ዋጋ የከፈሉ ጀግኖች ታሪክን አስጎብኝተናቸዋል” ብለዋል።

አክለውም፣ “ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ለነበራቸው ጊዜ እያመሰገንን፤ በምድረ ቀደምቷ ኢትዮጵያ እንዲሁም በውቧ መዲናችን አዲስ አበባ የሚኖራቸው ቆይታ ፍሬያማ እንዲሆን በራሴ እና በከተማ አስተዳደሩ ስም ከልብ እመኛለሁ” ማለታቸውም ይታወሳል። የእስራኤል ፕሬዝዳንት አይዛክ ሄርዞግ የዓድዋ ድል መታሰቢያ በተጨማሪ የሳይንስ ሙዚየምን እና ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ጉብኝተዋል፡፡

የኢትዮ እስራኤል ጉዳይ ዋነኛው የዚህ ፅሑፍ ማጠንጠኛ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ያላት የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የበለጠ እየተጠናከረ መጥቷል። ለአብነትም ከጥቂት ሳምንታት በፊት የህንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ፣ የቱርክዬ ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፐ ኤርዶዋን፣ የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና የሌሎች ሀገራት ከፍተኛ አመራሮች በኢትዮጵያ ይፋዊ የስራ ጉብኝት ማድረጋቸው ማሳያ ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች በተለያዩ ሀገራት የስራ ጉብኝት ያደርጋሉ። ለአብነትም ባሳለፍነው ሐሙስ በአዘርባጃን ይፋዊ የስራ ጉብኝት አድርገዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአዘርባጃን ያደረጉትን የስራ ጉብኝት አስመልክቶ በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ባስተላለፉት መልዕክት፣ “በአዘርባጃን ባደረግኩት የመጀመሪያ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ፕሬዝዳንት ኢልሃም አሊዬቭ ላደረጉልኝ ሞቅ ያለ እና የተከበረ አቀባበል ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ” ብለዋል።

አክለውም፣ “ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአቪዬሽን ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በነፃ የንግድ ቀጣናዎች፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና በአዘርባጃን አቻቸው መካከል በተደረጉ የኢኮኖሚ ትብብሮች ላይ በመመስረት አጋርነታችን በየጊዜው እያደገ መጥቷል። እነዚህ የትብብር ዘርፎች ለሁለትዮሽ ግንኙነታችን መጠናከር መሠረት የጣሉ ሲሆን፣ ዛሬ ባደረግነው ጥልቅ ውይይትም ግንኙነታችንን እና ትብብራችንን ይበልጥ ለማጠናከር እና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ተስማምተናል” የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

## ዓድዋ... ከገጽ 1 የዞረ

የዓድዋ ድል በውጫዊ የመሣሪያ፣ የፋይናንስ፣ የጦር ስትራቴጂ እና የሥልት ምክር የተደገፈ አልነበረም። ይልቅ የኢትዮጵያ ልጆች ራሳቸውን በራሳቸው ችለው የመሩት፣ አንድነት እና ከምንም በላይ ሀገርን ማስቀደም ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ያረጋገጡበት ድል መሆኑን የታሪክ ባለሙያው መክብብ ንጋቱ (ዶ/ር) ይናገራሉ።

የታሪክ ባለሙያው አክለውም ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ድል ያደረጉበትን ምስጢርን አስመልክቶ እንደገለጹት የዓድዋ ድል ትልቁ ምስጢር ውስጣዊ አንድነት ነው፤ በዳግማዊ ምኒልክ መሪነት ውስጣዊ አንድነትን በማጠናከር በአንድነት፣ በሙሉ ልብና በአሸናፊነት ስሜት ወደ ጦር ሜዳው እንዲዘምቱ ተሰርቷል፡፡

ይሁን እንጂ በወቅቱ ልዩነቶች የሉም ባይባልም ኢትዮጵያውያን ለሀገር ቅድሚያ በመስጠት ውስጣዊ አንድነታቸውን ከፍ አድርገው እንደ ሰርገኛ እየጨፈሩ፣ በጀግንነትም እየፎከሩ እግራቸውን ለጠጠር፣ ደረታቸውን ለጦር፣ ነፍሳቸውን ለእግዜር አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ በደም በተጻፈ ታሪካቸው ሀገር አትርፈዋል፡፡ በዓለም አደባባይም የኢትዮጵያውያንን መልክና ልክ በማይደበዝዝ ቀለም ስለዋል፡፡

በመሆኑም አዲሱ ትውልድ ከዓድዋ ብዙ የሚማራቸው ቁም ነገሮች እንዳሉ የጠቀሱት የታሪክ ባለሙያው፤ ለአብነትም ጥቃቅን ልዩነቶችን አግዝፎ ከመጣላት እና ውስጣዊ አንድነትን ከሚያላላ ነገር መቆጠብ አለበት፡፡

ሌሎች ሀገራት ዓድዋን እንደ ወርቅ በመቁጠር ተጠቅመውበታል፡፡ ነጻነታቸውንም ተጎናጽፈውበታል፡፡ እኛ ግን በልኩ ስላልተጠቀምንበት በትኩረት ልንሠራበት ይገባል፡፡ ለአብነትም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአዲስ አበባ የተገነባው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ለዚህ አንዱ ማሳያ እንደሆነም የታሪክ ባለሙያው መክብብ (ዶ/ር) ጠቅሰዋል፡፡

ከዓድዋ ድል ማግስት አውሮፓውያኑ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ተቀብለዋል፤ ዕውቅናም ሰጥተዋል፡፡ ለአብነትም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን እና መሰል ኃያላን ሀገራት በአዲስ አበባ ኤምባሲያቸውን ለመክፈት ተገድደዋል፡፡

እነዚህና መሰል ተግባራት ኢትዮጵያን በአፍሪካ ብሎም በዓለም አደባባይ ገናና ስም እንዲኖራት አድርገዋል፡፡ የዓድዋ ድል ለፓን አፍሪካኒዝም መሠረት ሆኗል፤ አፍሪካ አሜሪካውያንም ነጻነታቸውን አስከብረውበታል ብለዋል፡፡

በመሆኑም ይላሉ መክብብ (ዶ/ር)፤ ዘመኑን የሚመጥን ዝግጅት እና ውስጣዊ አንድነትን ማጠናከር ልክ እንደ ዓድዋ ለሁለንተናዊ ድል ያበቃል፡፡ በተለይም አርበኝነት ዘመኑ የሚፈልገውን ሆኖ መገኘት፣ ያጋጠመውን ችግር በእውቀትና ብልሃት አሸንፎም መውጣት ነውና ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ ድል ይህንን ሊማሩ ይገባል ብለዋል፡፡




ፎቶ- ከፋይል

የዓድዋ ድል መላው ኢትዮጵያውያን በመተባበራቸው የተገኘ ዘመን ተሻጋሪ ታሪካዊ ድል ነው

በመዳ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር እና ኮሙኒኬሽን መምህር ቴሶ በሪሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን አንድነትና ኅብረት ማሳያ ነው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ ድል ብዙ መማር አለብን። ይኸውም ለሀገር ክብርና ከፍታ ሲባል ልዩነትን በውይይትና በይቅርታ መፍታትን፣ በምትኩም አንድነትን ማጠናከር እና በጋራ በመቆም ሀገርን ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ከድሉ ብዙ ዕውቀትን መማር እንደሚቻልም ጠቅሰዋል፡፡

አክለውም ሀገር የምትገነባው የኋላውን በመያዝና ከሱም ትምህርት በመውሰድ ነው፡፡ ስለሆነም የዓድዋ ድል እንዴት እንደተገኘ? ሂደቱ ምን ይመስል እንደነበር እና የነበረው አደረጃጀትና የተከፈለው መስዋዕትነት ምን ያህል ከፍ ያለ መሆኑን በደንብ ማወቅና በዚያው ልክ ለሀገር ሁለንተናዊ ልዕልና መቆም ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ በአፍሪካውያን መዲና የተገነባው የዓድዋ ድል መታሰቢያም ትልቅ አጋዥ የሚሆን ነው ብለዋል፡፡

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ተማማ ሐጅ አደም (ዶ/ር) ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ እንደገለጹት ኢትዮጵያ ብዙ አሰባሳቢ ትርክቶች አሏት፡፡ ለአብነትም የዓድዋ ድል አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም የዓድዋ ድል ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በእምነት፣ በባህል እና በቋንቋ ሳይለያዩ ከሁሉም አቅጣጫ የተሳተፉበትና ታላቅ መስዋዕትነት ከፍለው ያስገኙት ድል ነው፡፡ አክለውም ድሉ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ የተነሱበትና ነጻነታቸውን ያስከበሩበት ነው፡፡ በመሆኑም ከምንም በላይ ሀገርን ማስቀደም ከዓድዋ ድል ልንማር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዓድዋ፤ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ አብረው የወደቁበትና በጽናት የቆሙበት ትልቅ ተምሳሌት በመሆንም ያገለግላል። ሁሌም ኢትዮጵያውያን ለአንድነታቸው መስዋዕት ለመሆን ዝግጁ መሆናቸውንም የሚያሳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የቆመችው በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና ሁለንተናዊ ማንነቶች ኅብረት ነው፡፡ የዓድዋ ድል ደግሞ ለዚህ ትልቅ ተምሳሌት በመሆኑ ትውልዱ ከዓድዋ በመማር ዘመኑ በሚፈልገው ልክ በተሰማራበት ሙያ ሁሉ ለሀገሩ መሥራት ይጠበቅበታልም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በሁሉም ተጋድሎ የጸናች ሀገር መሆኗን የዓድዋ ድል ያስተምረናል። የተማረም፣ ያልተማረም፣ ገበሬውም፣ ወንዶችም፣ ሴቶችም... ሁሉም የተሳተፉበት ነው፡፡ ይህም አንዱ ያለ ሌላው መኖር እንደማይችል የሚያሳይ ነው፡፡ ደስታና ድልን፣ ሐዘንና ችግርን በጋራ ተካፍሎ መቆምን የሚያሳይ ድል በመሆኑ ዓድዋ! ለኢትዮጵያውያን ጽናትና አንድነት፤ ለሀገራዊ ዕድገትና ከፍታ ትልቅ ድርሻ አለው ብለዋል ተማማ ሐጅ አደም (ዶ/ር)፡፡

አክለውም ዓድዋ ያኔ! የነበረው ሕዝብ በአንድነት በመቆሙ ያስመዘገበው ድል ነው፡፡ እንዲሁም ዓድዋ ኅብረ ብሔራዊነት የተገለጠበት የታሪክ አጋጣሚ ነበር፡፡ በመሆኑም የዛሬው ትውልድ ዓድዋን የመሳሰሉና ዘመኑን የዋጁ ድሎችን በአንድነት ማስመዝገቡን ይቀጥል ዘንድ ከጥቃቅን ጉዳዮች ወጥቶ እንደ ዓድዋ ከፍ ባለ ሐሳብ ላይ አንድ መሆን እንዳለበት መክረዋል፡፡

የዓድዋ ድል ከምንም በላይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቁርጠኝነት ቆሞ የባርነት ቀንበር እንዳይጫንበት የታገለበትና ድል የነሳበት ገድል ስለመሆኑም የታሪክ ባለሙያው መክብብ (ዶ/ር) አውስተዋል፡፡

እንደ መክብብ (ዶ/ር) ገለጻ፣ አሁን ያለንበት ድህነት፣ ጉስቁልና እና አልፎ አልፎ የሚስተዋል አለመግባባት ከዚህ ቀደም በዓድዋ ላይ ከገጠመን እና ድልም ከነሳነው ችግር የሚበልጥ አይደለም፡፡ ዛሬ እያጋጠመን ላለው ችግር በመደማመጥና በመነጋገር፣ በመመካከርና በመከባበር የማይፈታ ነገር ስለማይኖር አባቶቻችን እና እናቶቻችን ያሳለፉትን ያንን ትልቅ ውጣ ውረድ መለስ ብሎ በመመልከት ትውልዱ ለሌላ ድል ራሱን ማዘጋጀት እንዳለበት መክረዋል፡፡ በመሆኑም ከዓድዋ ድል በጋራ መቆምን፣ በጋራ ማቀድን፣ በጋራ መተግበርን መማር አለብን፡፡

ስለ ዓድዋ ከተጻፉ መጻሕፍት መካከል የዓድዋ ጦርነት (THE BATTLE OF ADWA) የተሰኘው መጽሐፍ አንዱ ነው፡፡ ይህንን ድንቅ መጽሐፍ ለሕትመት ያበቁት የታሪክ ተመራማሪዎቹ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት፣ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፣ ንጉሤ አየለ፣ ሃሮልድ ማርከስን የመሳሰሉ ጉምቱ የታሪክ ምሁራን ናቸው፡፡

በመጽሐፉ የዓድዋ ድል በጣፋጭ ቃላት ተውቦ ይታያል፡፡ ዓድዋ የድፍረት፣ የድል እና የኩራት ተምሳሌት እንደሆነም ተገልጿል፡፡ ኢትዮጵያ በአውሮፓ ኢምፔሪያሊዝም ላይ የተቀዳጀችው የዓድዋ ድል የሰው ልጆች ሁሉ እኩል መሆናቸውን በሚገባ ያረጋገጠ ዝንፍ የማይል መለኪያ ነው፡፡ ዓለማችን ግሩም የታሪክ እጥፋት ያስመዘገበችበት ወሳኝ የታሪክ ክስተትም ነው ዓድዋ!

ዓድዋ የዓለማችን ድንቅ የታሪክ ዘለላ ሲሆን፣ በተለይም የመላው አፍሪካውያን የጋራ ትውስታቸው ስለመሆኑም በመጽሐፉ የተለያዩ ገጾች በወጉና በልኩ ተመላክቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ዓድዋ በዘመን ጅረት ሳያረጅ ሰርክ አዲስ እንደሆነ እና ሁሌም እንደተከበረ በአፍሪካውያን ሰማይ ሥር እንደ ፀሐይ ፈክቶ ዓለምን በእኩልነት ፀዳል እያጥለቀለቀ በከፍታ የሚኖር ታላቅ ድል ስለመሆኑም ተጽፏል፡፡

በመጽሐፉ በግልጽ እንደተመላከተው ዓድዋ ከትውስታ በላይ ነው፡፡ ድል የተፈጸመበትን ዘመን ብቻ የሚናገር፣ ተደምጦም የሚቀር አይደለም፡፡ ይልቅ ዓድዋ ሁሌም እንደ ንጋት ኮከብ እያበራ እና በዓለም የታሪክ ምዕራፍ ላይ ሰርክ አዲስ እንደሆነ ይቀጥላል እንጂ፡፡ አዎ! ዓድዋ ጊዜውን የሚያንጸባርቅ ድል ብቻ ሳይሆን "የሰው ልጆች ሁሉ እኩል ናቸው!" እያለ በእውነት አደባባይ ከአድማስ አድማስ፣ ከዘመን ዘመን የሚመሰክር ድል ነው፤ ዓድዋ!

በእርግጥም በዓድዋ በተካሄደው ጦርነት ኢትዮጵያውያን በአንድነት ያደረጉት ተጋድሎና ያስመዘገቡት ድል የኢትዮጵያ ነጻነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ እንዲቀጥል ከማስቻሉም ባለፈ በወቅቱ በቅኝ ገዢዎች ተይዘው በባርነት ቀንበር ሲማቀቁ የነበሩ አፍሪካውያን ለሚያደርጉት የነጻነት ትግል ከፍተኛ መነቃቃት የፈጠረ ነው፡፡ በርካታ አፍሪካውያንና የታሪክ ጸሐፍትም የዓድዋ ድልን "የአፍሪካ ድል"፣ "የእኩልነትም ቀንዲል!" እያሉ ይጠሩታል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ እስከ ካራማራ ከጫፍ እስከ ጫፍ ሀገራቸውን በአጥንታቸው አጥረው አስከብረዋል፡፡ ሉዓላዊነትን እና ነጻነታቸውን ለማስጠበቅ ከተከፈለው ዋጋ ባልተናነሰ መልኩ ታላቁ የሕዳሴ ግድብን በመሳሰሉ ከፍ ከፍ ባሉ ልማቶች ያለምንም ልዩነት ተሳትፈው የአብሮነት ክንዳቸው ምን ያህል ብርቱ እንደሆነም አሳይተዋል፡፡

የታሪክ ባለሙያው መክብብ ንጋቱ (ዶ/ር) አክለውም ዛሬም ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ ድል ትምህርት በመውሰድ የሀገርን ሁለንተናዊ ልማትና ከፍታ በሚያረጋግጡ ልማቶችና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ በአንድነት በመቆም የሀገራችንን ሁለንተናዊ ከፍታ ማስቀጠል ይጠበቅብናልም ብለዋል፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በ8ኛው ሀገር አቀፍ የሰላምና ፀጥታ ምክክር መድረክ ላይ ንግግር አድርገዋል

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካውያን መናኸሪያ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፣ በዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችውን አዲስ አበባን ሰላምና ጸጥታዋን ዘላቂ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። የተለያዩ የጸጥታ አካላትንና ሕብረተሰቡን በማሳተፍ እና የጸጥታ ሥራውን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የሚሠራው ሥራ ከተማዋን ሰላማዊና ደህንነቷ የተጠበቀ እንድትሆን አስችሏል። ይህ ተሞክሮ ወደ ሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ሊሰፋ እንደሚገባ በትላንትናው ዕለት በጀመረውና በዛሬው ዕለት በሚጠናቀቀው ሀገር አቀፍ የሰላምና ጸጥታ የጋራ ምክክር መድረክ ተገልጿል።

8ኛው ሀገር አቀፍ የሰላምና ጸጥታ ምክክር መድረክ "ሰላማዊ ፖለቲካ ለሀገራዊ ብልጽግና" በሚል መሪ ሀሳብ በሰላም ሚኒስቴር እና በአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ በጋራ በመሆን በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው። በዓድዋ ድል መታሰቢያ እየተካሄደ ባለው የምክክር መድረክ ሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች፣ የፌዴራል ተቋማት እና ሌሎች የሰላምና ጸጥታ ባለድርሻ አካላት በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅት እያደረገች ባለበት ወቅት የተካሄደው የምክክር መድረኩ፤ የሕዝብ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነት መገለጫ የሆነው ምርጫ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ አሳታፊና ተአማኒነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫና በድህረ ምርጫ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሰላም ችግሮችን ለመፍታት ምክክር የሚደረግበት እንደሆነም ተገልጿል።

በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ በአዲስ አበባም ሆነ በመላ ሀገሪቱ ሰላምን ለማረጋገጥ ሕዝብን የሰላም ባለቤት ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ ተናግረዋል። ከንቲባዋ በይፋዊ የማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት "ሰላምን አስተማማኝና ዘላቂ ለማድረግ ሕዝብን የሰላም ባለቤት ማድረግ ወሳኝ ነው። በዚህ ረገድ መዲናችን አዲስ አበባ ስኬታማ ተሞክሮ ያላት በመሆኑ፣ ለሌሎችም ሰፊ ልምድ ታካፍላለች" ብለዋል።

"የዘላቂ ሰላም መስፈን ለልማት ሥራዎቻችን ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፤ የሁሉን አቀፍ ልማት መረጋገጥ ደግሞ በምላሹ አስተማማኝ ሰላምን ያሰፍናል" ያሉት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ አዲስ አበባ በሁለንተናዊ መልኩ ሕዝብን በማሳተፍ በምትሠራው ሥራ የሕዝብን ባለቤትነት መፍጠር እንደቻለች ተናግረዋል።

የሰላም ሚኒስትር አቶ መሐመድ እድሪስ በበኩላቸው አዲስ አበባ በልማትም ሆነ ሰላምና ጸጥታን በማስጠበቅ አርዓያ መሆኗን ተናግረዋል። በከተማዋ የሰላምና ጸጥታን የማረጋገጥ ሥራ ሕዝባዊ መሠረት

> **"የዘላቂ ሰላም መስፈን ለልማት ስራዎቻችን ስኬት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፤ የሁሉን አቀፍ ልማት መረጋገጥ ደግሞ በምላሹ አስተማማኝ ሰላምን ያሰፍናል።"**

እንዲኖረው የተሠራው ሥራ ከተማዋን ሰላምና ደህንነቷ የተረጋገጠ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማ መሆኑንና ይህንንም መልካም ተሞክሮ ሌሎች ክልሎችና ከተሞች ሊወስዱት ይገባል ብለዋል። በከተማዋ ከሚሠሩ የልማት ሥራዎች ጎን ለጎን በቴክኖሎጂ ታግዞ እየተከናወነ ያለው ሰላምን የማስፈንና ወንጀልን የመከላከል ሥራ ውጤታማ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ እንዲሁ በአዲስ አበባ በጸጥታ አካላትና በሕብረተሰቡ መካከል በቅንጅት በተሠራው ሥራ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ ተችሏል። በተለይ ሕብረተሰቡ በሰላም ሠራዊት በመሳተፍ የአካባቢውና የከተማዋ ሰላምና ጸጥታ እንዲረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ደረቅ ወንጀሎችን፣ ሰላምን ለማወክ የሚንቀሳቀሱ ሰርጎ ገቦችንና ጸጉረ ልውጦችን በመከላከልም ውጤታማ መሆን ተችሏል። በተጨማሪ ከአጎራባች ክልሎች በተለይ ከሸገር ከተማ አስተዳደር ጋር በቅንጅት በመሥራት የከተማዋን ሰላምና ጸጥታ አስተማማኝ ማድረግ ተችሏል። ባለፉት ወራት ሚሊዮኖች በአደባባይ ወጥተው ያለምንም የሰላምና ጸጥታ ችግር በዓላትን ማክበር መቻላቸው ለዚህ ማሳያ እንደሆነ አንስተዋል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ሁሉን አሳታፊ እና የሀገረ መንግሥት ግንባታውን የሚያጸና እንዲሆን መንግሥት በቁርጠኝነት እየሠራ እንደሚገኝ አንስተው፣ ምርጫ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ለመመሥረትና ዘላቂ የሆነ ሰላምና መረጋጋት የሚያመጣ በመሆኑ ለስኬታማነቱ ሁሉም ሊረባረብ እንደሚገባ ተናግረዋል። በኢትዮጵያ ለዘመናት የግጭት ምክንያት የሆኑ ልዩነቶችን ከምንጫቸው ለማድረቅ፣ የሕዝብን የሰላም እሴቶች ለማዳበር፣ በብሔራዊ ምክክር በመፍታት አስተማማኝ እና ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ የሁሉም እገዛ አስፈላጊ እንደሆነም አክለዋል።

በመድረኩ እንደተገለጸው አዲስ አበባን ልክ እንደ ስሟ ውብና አዲስ፣ ለነዋሪዎችና ጎብኚዎች የምትመች ከተማ ለማድረግ በተሠራው ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች እየጨመሩ መጥተዋል። በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ብቻ 150 አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች በአዲስ አበባ በሰላም ማከናወን ተችሏል። በዚህም የሀገርን መልካም ገጽታ መገንባት እንደተቻለ ተገልጿል። በከተማዋ የጸጥታ ሥጋቶችን አስቀድሞ አጥንቶ እርምጃ በመውሰድ፣ በኮሪደር ልማቱ ሰላምንና ጸጥታን፣ ወንጀልን ለመከላከል የሚረዱ ዘመናዊ የደህንነት ካሜራዎችን በመግጠም፣ ሕብረተሰቡን በማሳተፍ የተሠሩ ሥራዎች ሰላምና ደህንነቷ የተጠበቀ እንድትሆን በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል።

# የሀገራዊ ትርክት መሰረቶች

- **የኢትዮጵያውያን የማንነት መገለጫዎች ስነ ጥበባዊ በሆነ መልኩ መሰራታቸው አሰባሰቢ ትርክት ለመገንባት እንደሚያግዙ ተጠቁሟል**



ፎቶ- ከፋይል
በመዲናዋ ለወል ትርክት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ስራዎች በከፊል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ በሀገርና ዓለም አቀፍ ደረጃ የምትታወቅባቸው በርካታ መገለጫዎች አሏት፡፡ ጥንታዊነቷ፣ የሰው ዘር መገኛነቷ፣ በአፍሪካ በቅኝ ግዛት ስር ያልወደቀች ብቸኛ ሀገር መሆኗ፣ የቀን አቆጣጠሯንና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል። ብዝሃነቷም ሌላው መለያዋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ኢትዮጵያ ብሔርን፣ ታሪክን፣ ባህልን፣ ሃይማኖትን፣ ቋንቋን ጨምሮ የተለያየ ማንነት ያላቸው ህዝቦች ሀገር ናት፡፡ የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት ለማስጠበቅ በጋራ በመቆም መመከት ደግሞ የኢትዮጵያዊውያን የጋራ ማንነት መገለጫ ነው፡፡ በየዘመናቱ ከውጭ ወረራ ሲያጋጥማቸው በአንድነት ሆኖ አሳፍሮ በመመለስ የሀገራቸውን ሉዓላዊነትና ነጻነት አስጠብቀውና አጽንተው ዘልቀዋል፡፡ በዚህ ረገድ የዓድዋ ድል ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡

የታሪክ ተመራማሪው ኢብራሂም ሙሉሸዋ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ የዓድዋ ድል በአራቱም አቅጣጫ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የአመለካከት፣ የጾታና ሌሎች ልዩነቶች ሳይገድባቸው የዳግማዊ አፄ ምኒልክን የክተት አዋጅ በመቀበል ጠላትን ለመፋለም በጋራ የተመሙበት፤ የኢትዮጵያውያን የአብሮነትና አንድነት ማሳያ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በመካከላቸው ልዩነት እንኳን ቢኖራቸው ሀገር ችግር ሲገጥማት ወይም ስትደፈር እንዴት በአንድነት ጠላትን ለመከላከል እንደሚሰለፉ የታየበት ድል ነው፡፡

ተክለጻድቅ መኩሪያ "ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሀይለስላሴ" በሚለው መጽሀፋቸው ላይ፣ የአካባቢው መሳፍንት (አስተዳዳሪዎች) "...ዳግማዊ ምኒልክን እንደሸዋ ንጉስና እንደባዕድ ቆጥረው የራሳቸውን ምኞት በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ለመፈፀም በመሞከር ተለይተው ቢሆን ኖሮ ወይም እንሸፍት ብለው የውስጥ ግጭት ተነስቶ ቢሆን ኖሮ የጣሊያን ጦር ምን ያህል ይጠቅመው እንደነበር ግልፅ ነው። የጣሊያን የጦርና የፖለቲካ መሪዎች ውስጥ ለውስጥ እየተላላኩ ጆሯቸውን ከፍተው የጠበቁት ይህንን ነበር፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ አንድነት፣ የመኳንንትና የመሳፍንቱ ህብረት፣ የጦር ሰራዊቱ ታማኝነት ከመቼውም ጊዜ በላይ የጠበቀ ነበር" ሲሉ ለድሉ መገኘት የኢትዮጵያውያን በአንድነት መቆም የነበረውን ሚና አመላክተዋል፡፡

የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ነጻነት ተጠብቆ እንዲቀጥል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ በጦርነቱ ጣሊያን በማይቀለበስ መልኩ ሽንፈት ከደረሰባት በኋላ በአዲስ አበባ ስምምነት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት እውቅና ሰጥታለች፡፡ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮችም የኢትዮጵያን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ለማክበር ቃል ገብተዋል፡፡ ኢትዮጵያ በዓድዋ ባስመዘገበችው ድል ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ማእከል ልትሆን እንደቻለች የታሪክ ተመራማሪው ኢብራሂም (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

## እንደ ዓድዋ ያሉ ታሪኮች ለጋራ ትርክት ግንባታ እንዴት እንጠቀምባቸው?

ትርክት መግባባትና አንድነትን ማጠናከሪያ አሊያም ልዩነቶችን በማስፋት ወደ ግጭት የሚያስገባ መሳሪያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት "የትርክት ዕዳና በረከት" በሚለው መጽሀፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት በኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ህገ መንግስትና ፌዴራሊዝም እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ተቃራኒ ትርክቶች ይራመዳሉ፡፡ እነዚህም አንድነታችንና አብሮነታችን እንዳይጠናከር፣ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንድንዘፈቅ አድርገውናል፡፡

በተለይ ከሀገራዊ ለውጡ በፊት በነበሩት ሶስት አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ ሲቀነቀን የነበረው ነጠላ ትርክት በማህበረሰብ፣ በሊሂቃን መካከል መከፋፈል፣ ቅራኔ፣ አለመተማመን እንዲባባስ በማድረግ የሀገር ግንባታው ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳረፉን በጂማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ቅርስ አስተዳደር መምህር ኑሩ ይማም ይናገራሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ስልጣን ከመጡ ወዲህ የጋራ ትርክት መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ የጋራ ድሎች፣ የጋራ ቅርስ፣ ብዝሃ ባህል ሀብቶችን በመለየት የትርክት ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ገበታ ለሸገር በተሰሩ የአንድነትና የእንጦጦ ፓርኮች እና የወዳጅነት አደባባይ እንዲሁም ደግሞ በኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ እና ሌሎች ልማቶች የኢትዮጵያን መልክና ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ እሴት የሚያሳዩ መገለጫዎች በቅርፃ ቅርፅ፣ በስዕል፣ በጽሑፍና በተለያየ ስነ ጥበባዊ ቅርፅ ሳቢ በሆነ መልኩ ተካትተው ተሰርተዋል፡፡

የኢትዮጵያውያን የጋራ የድልና የከፍታ ምልክት ከሆኑ ታሪኮች መካከል ዋነኛው ዓድዋ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካና ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ችቦ ብርሃን የለኮሰ፤ የዓለም ታሪክን የቀየረውን ድል በልኩ መዘከር እንዲቻል በአዲስ አበባ እምብርት ግዙፍ መታሰቢያ ተገንብቷል፡፡

በወንዝ ዳርቻ ልማትም ለምሳሌ ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ በተሰራው የወንዝ ዳርቻ ከዓድዋ ድል መታሰቢያ ወረድ ብሎ የዓድዋ ዘማቾች የተሰባሰቡበት ቦታ አካባቢ፣ የሀገርን ዳር ድንበርና ነፃነት ለማስከበር ኢትዮጵያውያን ስንቅና የጦር መሳሪያ በፈረስ ላይ ሆነውና ጭነው፣ ጀግኖች አርበኞች ጋሻና ጦር ይዘው ጉዞ ሲያደርጉ የሚያሳዩ ሐውልቶች ቆመውና በግድግዳ ላይ በስዕል ተስለው ይታያሉ። ፈረሶች እንዲሁም ተራራማ በሆነው መልከአምድር የሚኖሩ ብርቅዬ ጭላዳ ዝንጀሮዎች በልዩ የስነ ጥበብ ተሰርተው ይታያሉ፡፡

ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ መተላለፊያ በሆነውና በዓድዋ ጦርነት ከተሳተፉ የጦር መሪዎች አንዱ በሆኑት ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የተሰየመው ጥንታዊ "የራስ መኮንን ድልድይም" ከጎን የመስታወት ድልድይ፣ ጀግኖች አርበኞች ይጠቀሙባቸው የነበሩ እንደ ጋሻና ጦር ያሉ ምልክቶችን አካትቶ በሚያምር ስነ ጥበባዊ ውበት ታድሶ ተሰርቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ "የኢትዮጵያ ማንሰራራት ማሳያ፡- የወንዝ ዳርቻ" በሚል ርዕስ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከወራት በፊት በተላለፈው ዘጋቢ ፊልም ላይ እንደተናገሩት፣ በአራዳ ፓርክ የዓድዋ ዘማቾችን ታሪክ የሚያሳዩ ሐውልቶች እንዲቆሙ የተደረገው ለቱሪስት መስህብነትና ትውልድ እንዲማርባቸው ታስቦ ነው፡፡ "ታሪካችንን ማቅለል አይገባንም፡፡ የጋራ ትርክት መገንቢያችን ነው፡፡ ዓድዋ ኢትዮጵያውያን አንድ በመሆን፣ ሀይል፣ አቅምና ሀሳባቸውን በማሰባሰብ ሀገራቸውን የታደጉበት፣ ዛሬ የምንኮራባትን ሀገር ያስረከቡን አበውና እመው በምን ሚስጢር ነው? የሚለውን ትውልዱ የሚማርበትን ሁኔታ ይፈጥራል" ብለዋል፡፡

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ልክ ቀፎው እንደተነካበት ንብ በጋራ ተሰባስበው ከጣሊያን ጋር በመፋለም ያስገኙት ድል ነው፡፡ የዓድዋ ድል ሁሉም የተሳተፈበት መሆኑ እንዲታወቅ መደረጉ እንደሀገር የጋራ የሆነ ስነ ልቦናዊ አንድነት እንዲኖረን ያደርጋል። ይህም የኢትዮጵያውያን አንድነትና ሰላም እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ የሀገር ኢኮኖሚ ያድጋል፡፡ በሀገር ላይ አደጋ ሲፈጠር በጋራ የሚቆም ህዝብ ይፈጥራል ሲሉ የታሪክ ተመራማሪው ኢብራሂም (ዶ/ር) ድሉን መዘከር የሚያስገኘውን ጥቅም ያስረዳሉ፡፡

የታሪክ መምህር ኑሩ ይማም በበኩላቸው በአዲስ አበባ አዳዲስ በተገነቡና በታደሱ ሙዚየሞች፣ በኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በፓርኮች የኢትዮጵያውን ማንነት መገለጫዎችን፣ ታሪኮችንና ጀግኖችን ስነ ጥበባዊ በሆነ መልኩ መሰራቱ አሰባሳቢ ትርክት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ያግዛል። አዲስ አበባን ውብና ፅዱ እንድትሆን ማድረግ ብቻ ሳይሆን በልዩነት ውስጥ አንድነትን ለማጠናከር ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ፡ - አንድ ከውጭ ሀገር የመጣ ቱሪስት አዲስ አበባን ሲጎበኝ በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ ቅርሶችን፣ ምልክቶችን፣ ታሪካዊ ሁነቶችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ መረዳት ይችላል፡፡ ኢትዮጵያውያንም በአንድ ቦታ ብዙ ታሪኮችን በአንድ ቦታ መረዳት እንዲችሉ በማድረግ እርስ በርስ እንዲተዋወቁ፣ እንዲከባበሩና አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ በር ይከፍታል፡፡

የታሪክ ተመራማሪው ኢብራሂም በበኩላቸው የጋራ ትርክት ለመገንባት የጋራ የሆኑ ታሪኮችን በአግባቡ በጥናትና ምርምር በመለየት አጉልቶ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያውያን በእድር፣ እቁብ፣ ሰርግ፣ ለቅሶ በመደጋገፍና በመረዳዳት ሲኖሩ የጋራ እሴት ገንብተዋል፡፡ እነዚህን በማጉላትና በመጠበቅ ለጋራ ትርክት ግንባታ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የሁሉም ኩራት የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በስኬት መጠናቀቅ በኢትዮጵያውያን መነሳሳት፣ ሌሎች የጋራ ነገሮችን አብሮ ለመጀመርና የጋራ ትርክት ለመገንባት ጥሩ መነሻ ይሆናል፡፡ የጋራ ትርክትና ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር እንደሚረዳ ታምኖበት እየተሰራበት ያለው ሀገራዊ የምክክር መድረክም በሀገራችን ህዝቦች መካከል ለልዩነት ምክንያት የሆኑ፣ አብሮነትን እየፈተኑ ያሉ ቅራኔዎችን ወደ ጠረጴዛ በማምጣት ብሔራዊ መግባባትን እውን ለማድረግ እንደሚያግዝ ምሁራኑ ጠቁመዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የሴቶችና ወጣት ሠራተኞች የስራ ሁኔታ በአስሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 (ክፍል 1)

በደርብ ምሳዬ (ዐቃቤ ሕግ)

## መግቢያ

ሴቶችና ወጣት ሠራተኞች ያለምንም ልዩነት በግል ዘርፉ ተቀጥረው መስራት አንዱ ሕገ መንግስታዊ መብታቸው መሆኑ ይታወቃል። በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የሚሸፈኑ ወይም የሚተዳደሩ ናቸው። ይሁን እንጂ ሴት ሠራተኞች በስራ ላይ ሲሰማሩ በቅድመና ድህረ ወሊድ ጊዚያት ከሚያውኩ ሁኔታዎች፣ ከከባድ ወይም ለጤና ጎጂ ከሆኑ ስራዎች መጠበቅ ስላለባቸው በሕግ ልዩ ከለላና ጥበቃ ተሰጥቷቸዋል።

ዕድሜው ከአስራ አምስት ዓመት በታች የሆነን መቅጠር እንደማይቻል ዓለም አቀፍ ሕግ እንዲሁም፤ ይህ አዋጅ ክልከላ አድርጓል። ሆኖም ግን ወጣት ሰራተኞች ዕድሜያቸው 15 ዓመት የሞላቸውና 18 ዓመት ያልሞላቸው ልዩ ከለላና ጥበቃ ተሰጥቷቸው በግል ዘርፍ ተሰማርተው የሚሰሩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣት ሰራተኞች የአካላዊና የስነ ልቦናዊ እድገታቸውን የሚመጥን በተለዩ ስራዎች እንዲሰሩ በማድረግ የመስራት መብታቸውን ለማስጠበቅ አዋጁ አስፈላጊ ነው።

ለሴቶችና ለወጣት ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 እንዲሁም ይህን አዋጅ የሚያስፈጽሙ መመሪያዎች በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጡ (የአሁኑ ሥራና ክህሎት ሚኒስተር) በመመሪያ ቁጥር 811/2013 እና በመመሪያ ቁጥር 813/2013 ልዩ ከለላና ጥበቃ ተደርጎላቸዋል።

### 1. ለሴት ሰራተኞች የተሰጣቸው ልዩ ከለላና ጥበቃ

ሴቶች በፆታቸው ምክንያት በማንኛውም ሁኔታ ልዩነት አይደረግባቸውም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት ወይም በሌላ ማናቸውም የጥቅማ ጥቅም ውድድር ከወንድ ጋር እኩል የመሰጠት መብት አላት።

- **በቅድመና ድህረ ወሊድ**

ነፍሰጡር የሆነች ሠራተኛ ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርመራ ለማድረግ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ የማግኘት እና ከመውለዷ በፊት ሐኪም እንድታርፍ ካዘዘ ከክፍያ ጋር እረፍት የማግኘት መብት ይኖራታል።

እንዲሁም የ30 ተከታታይ ቀናት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ፣ እንዲሁም ስትወልድ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ ለ90 ተከታታይ ቀናት የድሕረ ወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር የማግኘት መብት



አላት። በአዋጁ አንቀፅ 29(3) ወይም በራሷ ጥፋት ካልሆነ በስተቀር ነፍሰጡር በሆነችበት ጊዜና ከወለደችበት ቀን ጀምሮ በ4 ወር ጊዜ ውስጥ አሰሪዋ ከስራ ሊያሰናብታት አይችልም።

ማንኛውም አሰሪ ነፍሰጡር የሆነች ሠራተኛን ከምሽቱ 4 ሠዓት እስከ ንጋቱ 12 ሠዓት ባለው ጊዜ እንዲሁም የትርፍ ሠዓት ማሰራት አይችልም። እንዲሁም የምትሰራው ስራ ለራሷም ሆነ ለጽንሱ ጤንነት አደገኛ መሆኑ በሀኪም ሲረጋገጥ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ተመድባ እንድትሰራ ማድረግ አለበት። ይህን የሚጥስ አሠሪ ካለ በአዋጁና በሌሎች ሕጎች መሰረት ተጠያቂ የሚያደርገው ነው።

- **ከባድ ወይም ለጤና ጎጂ የሆኑ ወይም የመውለድ ሁኔታን ከሚያውኩ ስራዎች የመጠበቅ**

በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 87 ንዑስ አንቀፅ 3 ለሴቶች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጎጂ ናቸው ተብለው በሚኒስቴሩ /በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር/ የወጡ (የአሁኑ ሥራና ክህሎት ሚኒስተር) በሚዘረዝራቸው ሥራዎች ላይ ሴቶችን ማሰራት የተከለከለ ነው በማለት ይደነግጋል።

በዚህ መሰረት ሚኒስቴሩ "ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጎጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ሥራዎችን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 811/2013" ዝርዝር ማስፈፀሚያ በማውጣት ልዩ ጥበቃና ከለላ ሠጥቷቸዋል። የመመሪያው ዓላማ ሴት ሠራተኞች በሥራ ላይ ሲሰማሩ ከተለያዩ የስራ ላይ አደጋዎች እና ጤና ጉዳቶች ለመከላከል በተለይም ከባድ ወይም ለጤና ጎጂ ከሆኑ ወይም የመውለድ ሁኔታን ከሚያውኩ ሥራዎች መጠበቅ ነው።

"ለጤና ጎጂ የሆኑ ሥራዎች" ማለት ከሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ወይም ከሥራ ሂደት የሚመነጩና በሴት ሠራተኞች ላይ አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳት የማስከተል ውጤት ያላቸው ፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ስነ ሕይወታዊ፣ ኢርጉኖሚካልና ሳይኮሶሻል ጠንቆች ያሉባቸው ሥራዎች ወይም የስራ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

"የመውለድ ሁኔታን የሚያውኩ ሥራዎች" ማለት የስነ ተዋልዶ ጤና ችግር የሚያስከትሉ እና የፅንስ ተፈጥሯዊ ዕድገትን የሚያዛቡ ስለመሆናቸው በሳይንሳዊ ምርምር የተረጋገጠላቸው ካርሲኖጂክ ሙታጂኒክና ቴራቶጂኒክ ንጥረ ነገሮች ወይም የንጥረ ነገር ውህዶች አገልግሎት ላይ የሚውሉበት የሥራ ዘርፍ ነው።

ማንኛውም አሰሪ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ስራዎች ላይ ሴት ሠራተኞችን ቀጥሮ ማሰራት የተከለከለ ነው፡-

- በማዕድን ቁፋሮና ከመሬት በታች በሚካሄዱ ጥልቅ የጉድጓድ ወይም የዋሻ ቁፋሮ ሥራዎች፣
- ፀረ-ተባይና ፀረ አረም ውህዶችን በመቀመም፣ በመበጥበጥ፣ በመሙላት፣ በማሸግ እና በመርጨት ሥራዎች፣
- በእርሻ ማሳዎች ውስጥ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ኬሚካሎችን በመርጨት ሥራ ማሰማራት፣
- የአስቤስቶስና የአስቤስቶስ ውህድ ንጥረ ነገሮችን፣ በመፍጨት፣ በመሞረድ እና በስራ ላይ እንዲውል በማድረግ፣
- ጥልቅ ውሃ ወይም በቀላሉ ሊመረዝ የሚችል የፍሳሽ ውሃ ውስጥ ገብቶ መስራት።

ማንኛውም አሰሪዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩ የስራ ዘርፎችና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለተሰማሩ ሴት ሠራተኞች ዓመታዊ የጤና ምርመራ እንዲደርግላቸው ያደርጋሉ፡-

- ተስማሚ መቀመጫ በሌለበት ሁኔታ ለረዥም ሠዓት በመቆም የሚሰሩ ስራዎች፣
- በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ ከደምና ከሰውነት የውስጥ ፈሳሽ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ስራዎች፣
- የድንጋይ ወፍጮ /ካባ/ እና የድንጋይ ጠረባ ሥራዎች፣
- በመንገዶች ስራ ውስጥ አስፋልት/ሬንጅ የማፍላትና የመርጨት ሥራ፣
- የመፀዳጃ ጉድጓዶችና የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦዎች የማፅዳት ሥራ፣
- በስራ ባሕርያቸው ከፍተኛ ቅዝቃዜ /cold/ እና ከፍተኛ ሙቀት /hot/ ባላቸው የስራ ዘርፎች፣
- የንዝረትና ሰውነትን የማንዘፍዘፍ (Vibration) ባህርይ ያላቸው ሥራዎች

ይሁን እንጂ በነዚህ ስራዎች ላይ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ ሴት ሠራተኞች ማሰራት የተከለከለ ነው። በተጨማሪም በመመሪያ ቁጥር 811/2013 በአባሪ ሁለት የተዘረዘሩ ለስነ ተዋልዶ ጤና ችግር መንስኤ ለሆኑ ንጥረ ነገሮችና የንጥረ ነገር ውህዶች በቀጥታ የሚያጋልጡ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴዎች ነፍሰጡር ሠራተኞችና ከወሊድ በኋላ እስከ 6 ወራት ድረስ ለሚያጠቡ ሠራተኞች ማሰራት የተከለከለ ነው።

አንባቢዎቻችን ቀጣዩን ክፍል በሚቀጥለው ሳምንት ይዘንላችሁ እንቀርባለን፡፡

# የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት

- **በመላው ዓለም የሚኖሩ ጥቁርና ጭቁን ሕዝቦችን ታሪክ በመቀየር ረገድ የዓድዋ ድል ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ደስታ መብራቱ (ፕ/ር) በተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ፕሮግራም የአፍሪካ ቀጣና ምክትል ዳይሬክተር መሆንን ጨምሮ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል። በተለያዩ አጋጣሚዎችም በርካታ አገራትን የመጎብኘትና የማየት ዕድልም አጋጥሟቸዋል።

አግራሞትና ሐዘኔታ ከፈጠረባቸው የጉብኝት አጋጣሚዎች መካከል በሴኔጋል ጎር ደሴት ያደረጉት ይጠቀሳል። የጎር ደሴት በአትላንቲክ የባሪያ ንግድ ዘመን (ከ16ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን) አፍሪካውያን በባርነት ወደ አሜሪካና ካሪቢያን ደሴቶች እስኪሄዱ ድረስ በእስር የሚቆዩበት የማሰቃያ ስፍራ ነው። ደስታ (ፕ/ር) አብረዋቸው ሲጎበኙ ከነበሩት አብዛኞቹ ከሰሜን አሜሪካ የመጡና አያቶቻቸው ከምዕራብ አፍሪካ የተለያዩ አካባቢዎች ታፍነው በባርነት የተሸጡ መሆናቸውን የሚያውቁ ናቸው። ስለሆነም የቀደምት አያቶቻቸውን የመከራና ስቃይ ጉዞ ተሸክመው በከፍተኛ ድባቴ ውስጥ ይጎበኙ እንደነበር "የትውልድ ውርስ፤ ከመተሐራ እስከ ፓሪስ" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ላይ አስፍረዋል።

"የባሕሩን ጉዞ ተቋቁመው ጥሩ ዋጋ ሊያወጡላቸው የማይችሉትን አፍሪካውያን የሚያስወግዱበት መንገድ፣ እጅና እግራቸው ታስሮ ወደ አሜሪካ እስከሚጓዙ ድረስ የሚቆዩበት ምድር ቤት ውስጥ ምግብ የሚመገቡበትና የሚጸዳዱበት ሁኔታ እና በመጨረሻም ወደ አሜሪካ የሚወስዳቸው መርከብ ላይ የሚሳፈሩበትን ቀጭን የሲኦል ቦይ ሲመለከቱ የሚሰማዎት የመንፈስ ስብራት እና ቁጣ በቃላት ለመግለጽ ያስቸግራል" ይላሉ ደስታ (ፕ/ር)።

በዚህ እንደ ሰው ልጅና አፍሪካዊነት ጥቅል ሐዘን እንደተሰማቸው የሚገልጹት ደስታ (ፕ/ር)፣ መንፈሳቸው ጠንካራ እንዲሆንና እንዲጸናኑ የሚያደርጋቸው አያት ቅድመ አያቶቻቸው ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪ ኃይል ለመጠበቅና ለመከላከል የከፈሉት መስዋዕትነት በማስታወስ እንደሆነ አክለው አስፍረዋል።

አዎ! ኢትዮጵያውያን የአገርን ነፃነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ የከፈሉት መስዋዕትነት በዋጋ የሚተመን አይደለም። በየዘመናቱ በከፈሉት መስዋዕትነት የኢትዮጵያ ነፃነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ ዘልቋል። ኢትዮጵያ ከራሷ ባሻገር አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ቀንበር እንዲላቀቁ፣ በመላው ዓለም የሚኖሩ ጥቁርና ጭቁን ሕዝቦች ነፃነታቸውን እንዲጎናጸፉና መብታቸውን ለማስከበር እንዲነሳሱ ተምሳሌት መሆን ችላለች። የኢትዮጵያን፣ የአፍሪካን፣ በመላው ዓለም የሚኖሩ ጥቁርና ጭቁን ሕዝቦችን ታሪክ በመቀየር ረገድ የዓድዋ ድል ትልቁን ሚና ተጫውቷል።

የታሪክ ተመራማሪው ኤርሚያስ ጉልላት (ዶ/ር) "የዓድዋ ጦርነት እና የዓለም ቅኝ ግዛት አሰላለፍ" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት፣ አፍሪካውያን በአትላንቲክ የባሪያ ንግድ ዘመን (ከ16ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን) ለ300 ዓመታት ሰብአዊ ክብራቸው ተዋርዶ እንደ እንስሳ ተቆጥረው፤ እንዳይጠፉ በሰንሰለት ታስረው ይሸጡ ነበር። አውሮፓውያን ቅኝ ገዥዎች "ነጮች የተለዩ ሕዝቦች ናቸው፤ የሰው ልጆች በአፈጣጠራቸው የተለያዩ ናቸው፤ ነጮች ከጥቁሮች የተለዩ ምርጥ ዘሮች ናቸው" የሚለውን የእንግሊዛዊ ሳይንቲስት ቻርለስ ዳርዊንን የፍጥረታት አመጣጥ (The Origin of Species) እሳቤ በመከተል ብዝበዛና ቅኝ ግዛቱን ተገቢ እንደሆነ አድርገው ይወስዱት ነበር።


ፎቶ- ከፋይል
የታሪክ ተመራማሪው አየለ በከሪ (ፕ/ር)

አየለ በከሪ (ፕ/ር) የታሪክ ተመራማሪ ናቸው። ለአሥራ አራት ዓመታት ያህል በአሜሪካ ኮርኔል ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ጥናትና ምርምር ማዕከል የአፍሪካ ታሪክ፣ ሥልጣኔና ባሕል ዙሪያ እንዲሁም መቀሌ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ታሪክ አስተምረዋል። እሳቸው እንደሚናገሩት፣ በፈረንጆች አቆጣጠር በ1885 አውሮፓውያን በበርሊን በመሰባሰብ አፍሪካን እንደ ቅርጫ በመከፋፈል በርካታ የአፍሪካ አገራት በቅኝ ግዛት ሥር አደረጉ። ኢትዮጵያንም ጣሊያን በቁጥጥሯ ሥር ለማዋል ስትነሳ በቀላሉ እንደምታሸንፍ በቅኝ ገዥ አውሮፓውያን ዘንድ ታምኖ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን በሚገባ በመደራጀት፣ 'አገር የሞተ እንደሆነ ወዴት ይደረሳል' በሚል እሳቤ በተባበረ ኃይል በመፋለም አሸነፉ።

ኢትዮጵያ በማይቀለበስ መልኩ ጣሊያንን ያሸነፈችበት የዓድዋ ጦርነት የራሷ ነፃነት፣ ሉዓላዊነትና አንድነት ተጠብቆ እንዲቀጥል ከማስቻል ባለፈ በአፍሪካና በመላው ዓለም በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ አገራት የፀረ ቅኝ አገዛዝ ተጋድሎ እንዲፋፋምና ነፃነታቸውን እንዲያገኙ በር ከፈተ። 'ኢትዮጵያውያን ቅኝ ሊገዛቸው የመጣውን ጠላት አሸንፈዋል፤ እኛም ቅኝ ገዥዎችን በመታገል ድል ማድረግ እንችላለን' በማለት እንዲነሳሱ ምክንያት እንደሆነ አየለ (ፕ/ር) ያስረዳሉ።

የታሪክ ተመራማሪው አየለ (ፕ/ር) እንደሚገልጹት፣ ዓድዋ አፍሪካውያንና መላው ጥቁሮች ከሰው በታች እንደ እንስሳ፣ ተሸናፊ፣ ደካማ፣ የማያስቡ ተደርገው የሚታዩበትን የተዛባ አመለካከት ቀይሯል። በአትላንቲክ የባሪያ ንግድ ዘመን ጥቁሮች እንደ ሰው አይቆጠሩም ነበር፤ ከእንስሳትና ዕቃ እኩል ተቆጥረው በባርነት ይሸጡ ነበር። በቅኝ ግዛት ዘመንም ሀብታቸውን ከመበዝበዝ ባሻገር በሐሰት ትርክት ዝቅ ተደርገው ይታዩ ነበር፤ ለተመሳሳይ ሥራ አነስተኛ ደመወዝ እየተከፈላቸው፣ ረጅም ሰዓት እንዲሠሩ እየተደረገ መብታቸው ተገፍፎ በተለያየ መልኩ ይጨቆኑ ነበር። የዓድዋ ድል በአፍሪካውያንና ጥቁር ዘሮች ላይ ይራመዱ የነበሩ የተዛቡ አስተሳሰቦች እንዲቃኑ አድርጓል። አፍሪካውያን ከነጮች ጋር እኩል እንደሆኑ፣ ማሰብ፣ መሥራት፣ ማሸነፍ እንደሚችሉና አላግባብ ይሰጣቸው የነበረ አተያይ እንዲቀየርና ተገቢ ያልሆኑ የመብት መነፈጎች እንዲቀሩ ምክንያት ሆኗል።

የታሪክ ተመራማሪው ኤርምያስም (ዶ/ር)፣ በመጽሐፋቸው "የዓድዋ ጦርነት በአካል በሥጋ በገሃድ ፍልሚያው የተካሄደው በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ነበር። የዓድዋ ጦርነት በመንፈስ የተካሄደው በዓለም ጥቁር ሕዝቦችና በአውሮፓ ቅኝ አገዛዝ ኃይሎች መካከል ነበር" ሲሉ አስቀምጠዋል። አክለውም በዓድዋ ጦርነት የተገኘው ድል የአፍሪካ ድል ነው። የአውሮፓ ቅኝ ግዛት መመሪያ የበርሊን ጉባኤ እንዲፈረካከስ ያደረገ ድል ነው። የሰው ልጅ እኩልነት የታየበት ሲሆን አፍሪካውያን ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ እንዲታገሉ ያነሳሳ ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ ነበር።

የዓድዋ ድል የመላው ጥቁር ሕዝቦችና የአፍሮ አሜሪካውያን ካሪቢያን ድል ነው። ከአፍሪካ ቅኝ ግዛት እንዲወገድና ነጭ መሸነፍ እንደሚችል አስተምሯል። የአውሮፓ ቅኝ አገዛዝ ከመላው አፍሪካ፣ ላቲን አሜሪካ፣ እስያ፣ ካሪቢያን ደሴት እንዲወገድ ያደረገና ጥቁር ሕዝቦችን የቀሰቀሰ እንደሆነም አስፍረዋል።

የታሪክ ተመራማሪው አየለ (ፕ/ር) እንዳብራሩት፣ በቅኝ ግዛት ዘመን እንደ አልጀሪያ፣ ማሊ፣ ኬንያ፣ ጋና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ታንዛኒያና ሌሎችም የአፍሪካ አገራት ቅኝ ግዛትን ለማስወገድ ትግል ሲያደርጉ ነበር። የዓድዋን ጦርነት ልዩ የሚያደርገው የተገኘው ድል ውጤቱ የማይቀለበስ ስለነበር፣ አፍሪካውያንና በመላው ዓለም የሚኖሩ ሕዝቦች ተስፋ ባለመቁረጥ ለነፃነትና እኩልነት ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ተምሳሌት መሆኑ ነው። ኢትዮጵያውያን 'እኛ ባሪያ የምንሆን ሕዝቦች አይደለንም፤ ሁለተኛ ዜጋ፣ የቅኝ ገዥዎች አገልጋይ አይደለንም' ብለው በመነሳት፣ ስልትና ስትራቴጂ በመቀየስ፣ ጠላትን ሲደመስሱ፣ የደመሰሱት ኢ-ፍትሐዊነትን፣ አድሎአዊነትን፣ አንዱ የበላይ ሌላውን የበታች የሚያደርገውን አመለካከት ነው። በዚህ ደረጃ ሲታይም ዓድዋ ጥልቅ የሆነ ፍልስፍና ነው።

አሜሪካዊው የታሪክ ተመራማሪ ራይሞንድ ጆናስ (ፕሮፌሰር) "የዓድዋ ድል" በተሰኘው መጽሐፋቸው በዓድዋ ጦርነት ጣሊያን በዘመናዊ እና እስከ አፍንጫዋ በታጠቀ ጦር ኢትዮጵያን ለመውረር ብትሞክርም፤ ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ወኔና መስዋዕትነት ጦርነቱን አሸንፈዋል። የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያንና የአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን የዓለምንም ቀጣይ የፖለቲካ አቅጣጫ የቀየረ ነው ብለዋል።

"በታሪክ ጥቁር ሕዝቦች ነጭ ወራሪን እስከመጨረሻው ድል ያደረጉበት የመጀመሪያው ክስተት ነበር። አፍሪካውያን ብቻ ሳይሆኑ አሜሪካውያንን ጨምሮ ሌሎች የቅኝ ግዛት ሰለባ አገራት በዓድዋ ድል በተፈጠረ መነሳሳት ምክንያት ፀረ ቅኝ ግዛት ትግል ጀምረዋል። ከድሉ በኋላ ቅኝ ገዥዎችም የግዛት ማስፋፋታቸውን ገትተዋል" በማለት ነው የገለጹት።

በጥቅሉ ዓድዋ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ከተመዘገቡና የዓለምን አካሄድ ከቀየሩ ክስተቶች መካከል አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል። ዓለም አፍሪካውያንን፣ በመላው ዓለም የሚኖሩ ጥቁርና ጭቁን ሕዝቦችን ይመለከትበት የነበረውን የተዛባ አተያይ የቀየረ እንደሆነ የታሪክ ማስረጃዎች ያሳያሉ። ኢትዮጵያ በዓድዋ ድል የተነሳ በአፍሪካውያንና በመላው ጥቁር ሕዝቦች ዘንድም የላቀ ቦታ እንዲሰጣት አድርጓል። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የአፍሪካ ሕብረት ዋና መስሪያ ቤት መቀመጫ፣ የተለያዩ ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መሰባሰቢያ እንድትሆን በማድረግ ረገድ ድሉ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

# አርበኝነት በየፈርጁ

በሄለን ጥላሁን

አጥንት ከስክሶ፣ ደምን አፍስሶ ሀገርን በመገንባት ሂደት ውስጥ የአርበኞች ሚና በታሪክ ውስጥ ትልቁን ድርሻ ይይዛል። የአርበኛነት መገለጫው በጦር ሜዳዎች ላይ የሚካሄዱ ውጊያዎችን መፈጸም ብቻ ሳይሆን፤ ሀገርን ከድህነት የተላቀቀች እና ለተተኪው ትውልድ የምትመች አድርጎ በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባትንም ያካትታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ዘመኑን የዋጀ የአርበኝነት ገድል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ ጽሑፍ በጉዳዩ ዙሪያ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን አስተያየት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



የኮንጎ ዘማች አሰፋ አዱኛ

## ሁሉም በተሰማራበት የሥራ መስክ ሀገርን በሀቀኝነትና በታማኝነት ማገልገል ይኖርበታል

የ1950ዎቹ እና 60ዎቹ የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ከሠራው ድንበር ተሻጋሪ ጀብዱዎች መካከል አንዱ በሆነው "የኮንጎ ዘመቻ" ላይ በክቡር ዘበኛነት ተሳትፌአለሁ፡፡

በልዩ ወታደራዊ ብቃትና ዲሲፕሊን በታከለበት አግባብ ተልዕኳችንን በማስፈፀም ረገድ ወሣኝ ሚና ለመጫወት ከቻሉት መካከል አንዱ ነኝ። በየዘመናቱ የሚፈፀሙ የአርበኛነት ታሪኮቻችን ውስጥ ትልቅ አቅም የሚሆነን በልባችን የሀገራችንን ሰንደቅ ዓላማ አትመን ማስቀመጣችን ነው፡፡

የጥንት አባቶቻችንና እናቶቻችን የአርበኝነት ታሪክ በደማቁ በደም አሻራ የተከተበ ነው። በጠላት ባህልና ወግ እንዳንተበተብ፣ በራስ ማንነታችን አሸብርቀን በኩራት ከአንገታችን ቀና ብለን ለመሄድ ምክንያት ሆነውናል፡፡

አርበኛነት ለሀገር እና ሕዝብ በሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ መሳተፍን ያካትታል፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ በቆመበት ቦታ የሚያደርገው አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሀገርን ትንሳኤ እውን በማድረግ ረገድ እገዛው ትልቅ ነው፡፡ ወቅቱ የሚፈልገው አርበኝነት፤ ሁሉም በተሰማራበት የስራ መስክ ሀገርን በሀቀኝነትና በታማኝነት ማገልገልን ነው፡፡ ይህንንም በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል፡፡



ወጣት ዮሴፍ ለገሰ

## አርበኝነት ማለት ሀገርን በሚያስከብርና በከፍታ ላይ በሚያስቀምጡ ተግባራት ላይ መሳተፍ መቻልን ያመላክታል

ለስልጣኔ መነሾ በሆንባቸው ዘመናት ለዓለም የሚጎበኙ ቅርሶችን በማስተዋወቅ አንድ ብለን የጀመርነውን ስራ አሁንም ማስቀጠል ይጠበቅብናል፡፡

አርበኝነት ማለት ለእኔ "ሀገርን በሚያስከብርና በከፍታ ላይ በሚያስቀምጡ ተግባራት ላይ መሳተፍ መቻልን" ያመላክታል። ሰው ሰራሽ አስተውሎትን በመጠቀም በርካታ ስራ አቅላይ ተግባራትን ለመከወን የሚቻልበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡

ከዓለም ጋር እኩል ለመራመድ በምናደርገው ጥረትም መንግስት አምስት ሚሊየን የኮደርስ ሰልጣኞችን በነፃ በማሰልጠን መሰረታዊ እውቀትን ለመሸመት በሚያስችል አግባብ እድሎችን አመቻችቶ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

እንደነዚህ ያሉ እድሎችን በመጠቀምና የራስን ጥረት በማከል ለሀገር አንድ እርምጃ የሚያራምድ ስራ መሰራት ይኖርበታል።

ፍላጎቶቻችንን መሬት የወረደ ስራ በመስራትና ለተግባራዊነቱ በመጣር ለሀገር ያለንን ፍቅር በአርበኝነት መንፈስ ማጠናከር ይገባል ባይ ነኝ፡፡

ፎቶ፦ በገነት ወንድሙ



ወ/ሮ አሰለፈች ቦኮ

## አርበኝነት፡- በተባበረ አቅም ጠንካራ ሀገር መፍጠር መቻል ነው

የጥንት አባቶቻችን እና እናቶቻችን የሀገርን ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ረገድ የከፈሉት መስዋዕትነት ትልቅ የአርበኝነት ተግባር ነው። እኛም ይህን መድገም ይጠበቅብናል፡፡

በዚህ ረገድም የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ፣ ውጤቶችም እየተመዘገቡ ነው፡፡

የጋራ የድል ታሪካችንን አንድ ሁለት ብለን ስናነሳ በቅርቡ ከፍፃሜ ያደረስነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ተጠቃሽ ነው፡፡

አርበኝነት ለእኔ የጋራ በሚያደርጉ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣ እውቀት ያለው በእውቀቱ በተባበረ አቅም ጠንካራ ሀገር መፍጠር መቻል ነው።

ሀገረ መንግስት በተጠናከረ አግባብ ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ ሁሉም በተሰማራው የስራ መስክ ውጤታማ ስራ መስራት ይጠበቅበታል።

በተለይም ባለጉዳዩን ከማጉላላት እና ባልተገባ ስነ ምግባር ከማስተናገድ ይልቅ ትህትና በተላበሰ አግባብ አገልግሎት መስጠት አንዱ የአርበኝነት መገለጫ ነው፡፡

በተለይ ደግሞ ከውጭ ሀገራት በሚደረገው ድጎማ ላይ ከመንጠልጠል ይልቅ በራስ አቅም ችግሮችን ቀርፎ ለመውጣት የሚደረገውን ትኩረት አሁን ላይ በስፋት ይስተዋላል። ታድያ እኔም እንደ አንድ ዜጋ ሀገራችን ከድህነት እንድትላቀቅ የበኩሌን ጥረት እያደረግኩ ነው፤ እሱን አጠናክሬ እቀጥላለሁ፡፡



ወጣት ዳግማዊ ገነነ

## 'ይሄ ስራ ለነገ ይሁን' ብሎ የማያሳድር ኢትዮጵያዊ ለእኔ አርበኛ ነው

አርበኛነት ማለት በእኔ አረዳድ ለሀገራችን ያለን መሰጠት፣ ፍቅር፣ መዋደድ እንዲሁም እርስ በእርስ መተሳሰብ የሚለውን ትርጉም ይይዛል፡፡ የአርበኛነት መገለጫዎቹ እጅግ ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡

በተለይ የኛ የኢትዮጵያውያንን የጀግንነት ታሪክ ያወሳን እንደሆነ የዓድዋ ድል የጀግንነት ታሪካችን ነው፡፡ ብርቱ ሃያላንና የሀገር ፍቅር ስሜት ውስጣቸው የሞላ አርበኞች የሚገኙባት ሀገር መሆኗን ከግምት ውስጥ ማስገባት ሳይችል አሰፍስፎ የመጣው ጠላት ውርደትን እንዲከናነብ አድርጎታል፡፡

ይህ ዘመን በመሰረታዊነት በቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚው፣ በምግብ ራስን መቻልን የሚጠይቅ ነው፡፡

የምዕራባውያንን ደጅ መጥናት እና ከልመና አዙሪት አለመውጣት በራሱ በጦር አውድማ ላይ ከመሸነፍ የተናነሰ አይደለም፡፡ በኛ ዘመን ወቅቱ ከሚፈልገው የአርበኝነት ጀብዱ መካከል የአምራች ኢንዱስትሪውን በመደገፍ ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ምርቶችን መተካት አንዱ ነው፡፡

ይህ ሲባልም ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶች እንዲመረቱ ከማድረግ አንፃር እንደ አዲስ አበባ ከተማ የተጀመሩ እንደ ኢትዮጵያ ታምርት ያሉ መርሃ ግብሮችን በመደገፍ የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ ያስፈልጋል።

"ደከመኝ ሰለቸኝ፤ ይሄ ስራ ለነገ ይሁን ብሎ የማያሳድር ኢትዮጵያዊ ለእኔ አርበኛ ነው፡፡

# የኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ጥቁምታ

**በአብርሃም ገብሬ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መርሃ ግብር መቅረባቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ከተሰናዱ መካከልም የስዕል አውደ ርዕይ እና የመጽሐፍት ውይይት ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡


## መጻሕፍት


በደራሲ ሮማን ገብረመድህን በተጻፈው ዮዲታ ግለታሪክ መጽሐፍ ላይ ዛሬ ከ8፡00 ሰዓት ጀምሮ ውይይት ይካሄዳል፡፡ ውይይቱን ያሰናዳው ዛጎል የመጻሕፍት ባንክ ሲሆን የውይይቱ አዘጋጅና አቅራቢ ደግሞ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ነው።

ውይይቱ የሚካሄድበት ሥፍራ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) አዳራሽ ሲሆን፣ ቀበና ካቶሊክ፣ ኪዳነምሕረት ቤተክርስቲያን አቅራቢያ፣ ወደ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት በሚወስደው መንገድ፣ ባማ አዲስ ሕንፃ አጠገብ ይገኛል፡፡

በሌላ መረጃ አንጋፋው ደራሲ ሲሳይ ንጉሱ፣ ከረዥም ዓመታት ቆይታ በኋላ “ሳልሳዊ ልደት” የተሰኘ አዲስ የመጽሐፍ ስራውን ለንባብ ሊያበቃ መሆኑን ኤሸንት አዲስ ሚዲያ ዘግቧል። ደራሲው በተለይም በታዋቂው “ሰመመን” ልብ-ወለድ መጽሐፉ በብዙዎች ዘንድ የሚታወስ ሲሆን፣ በተጨማሪም “የቅናት ዛር”፣ “ረቂቅ አሻራ” እና ሌሎች ተወዳጅ መጽሐፍትን ለንባብ ማብቃቱ ይታወሳል።







ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የጥበብና የሐሳብ ውይይት

“የቶሪኖው ግብዣና የሚጨሰው ጠረጴዛ” ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡ ነገ የዓድዋ ድልን ምክንያት በማድረግ ከዓመት በፊት በጣሊያን ቶሪኖ በቀረበው “የሚጨሰው ጠረጴዛ” በተሰኘው የሥነ ጥበብ ሥራ ላይ ነው ውይይት የሚካሄደው፡፡ ይህን የሥነ ጥበብ ስራ አዘጋጅቶ ያቀረበው እውቁ መምህር፣ ቀራጺና ሰዓሊ ፕሮፌሰር በቀለ መኮንን ነው፡፡ በዚህ ዝግጅት ላይም የመነሻ ሐሳብ የሚያቀርበው ራሱ ፕሮፌሰር በቀለ መኮንን ይሆናል፡፡ የጥበብና የሃሳብ ውይይቱ የሚጀምረው ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ ሲሆን፣ ውይይቱ የሚደረግበት ቦታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት (ወመዘክር) መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡ ያሰናዳው ደግሞ የዐውደ ፋኅስ የውይይት ክበብ ነው።

## የስእል አውደ ርእይ


“አደይ አበባ” የስዕል አውደ ርዕይ በዛሬው ዕለት ለእይታ ይበቃል፡፡ በገብረ ክርስቶስ ደስታ ዘመናዊ የሥነ ጥበብ ማዕከል በይፋ የሚከፈተው ይህ አውደ ርዕይ፣ በተለያዩ ጊዜያት የተሳሉ ሥዕሎች ለጥበብ አፍቃሪያን የሚቀርቡበት ነው ተብሏል፡፡ በሰዓሊ ጀርማይ ሚካኤል ተዘጋጅቶ ለዕይታ የሚያቀርበው ይህ አውደ ርዕይ፤ ሰዓሊው በአለ የሥነ-ጥበብ ትምህርት ቤት በነበረው ቆይታ ከሌሎች ከያኒያን፣ ተማሪዎችና የጥበብ አፍቃሪዎች ጋር በነበረው ማኅበራዊ መስተጋብር ያዳበራቸውን የፈጠራ ሥራዎች ያካተተ ነው ተብሏል። ከቀኑ 10፡00 ሰዓት የሚከፈተው ይህ መርሃ ግብር እስከ መጋቢት 12 ቀን ድረስ ለጥበብ አፍቃሪያን ክፍት ሆኖ እንደሚቆይ ታውቋል።

በሌላ መረጃ 7 ሰዓሊያን የተሳተፉበት “ዓድዋ” የተሰኘ የቡድን የስእል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ አውደ ርእዩን ያዘጋጁት አኑማ ሃይሉ፣ የሱቃል ተስፋዬ፣ ዮርዳኖስ ውቤ፣ እዮብ እሸቱ፣ ሱራፌል ከተማ፣ ዮዲት ወልደማርያም እና ዘካሪያስ ከተማ ናቸው፡፡ ፈንድቃ የባህል ማዕከል እና ሀያት ረጀንሲ ሆቴል በመተባበር ያዘጋጁት ይህ መርሃ ግብር እስከ የካቲት 30 ቀን 2018 ዓ.ም በእይታ ላይ ይቆያል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ


## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው $(6 + 15 + 19) - (7 + 11 + 10) = 12$ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ $(17 + 19 + 2) - (14 + 16 + 2) = 6$ ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት ሦስተኛውና የመጨረሻው $(11 + 7 + 5) - (3 + 8 + 2) = 10$ ይሆናል። ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **8** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አዲስ ስጦታ

- **ሚዲያው ‘ቡቤ’ የተሰኘ ሲትኮም ድራማ ወደ ተመልካች ሊያደርስ ነው**

**በጊዜው አማረ**

በዘመናዊው ዓለም የትልልቅ ከተሞች ህይወት ያለ ሚዲያና መዝናኛ ሊታሰብ አይችልም። ከተማ ማለት የሕንፃዎች ስብስብ ብቻ ሳትሆን የባህል፣ የንግድ፣ የፖለቲካና የፈጠራ ስራዎች መገናኛ ማዕከልም ናት። በዚህ መገናኛ ውስጥ ደግሞ የሜትሮፖሊታን ሚዲያ በመረጃ እና መዝናኛ ከመኖሪያ ቤታችን ይደርሳል።

የሜትሮፖሊታን ሚዲያ ማለትም ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጦችና የዲጂታል ገጾች የከተማውን ነዋሪ ስሜትና ፍላጎት የሚያንፀባርቁ ናቸው። የመዝናኛ ፕሮግራሞች ደግሞ የሜትሮፖሊታን ዋነኛ ክፍሎች ናቸው።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም የአዲስ አበባን ፈጣን የለውጥ ጉዞና የነዋሪውን ሁለንተናዊ ፍላጎት መሰረት በማድረግ፣ የሜትሮፖሊታን ሚዲያነቱን የሚመጥኑ ዘመናዊ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆኖ ብቅ ካለ ሰነባብቷል። ተቋሙ የከተማዋን ገጽታና የነዋሪዎቿን የአኗኗር ዘይቤ የሚያንፀባርቁ ልዩ ልዩ የጥበብ ስራዎችን ለተመልካች በማቅረብ፣ የአዲስ አበባን የባህል ማዕከልነት በይበልጥ እያደመቀ፣ የትውልድ ድምጽነቱን እያሳየና የሜትሮፖሊታን ሚዲያነቱን በተግባር እያሳየ ይገኛል። ይህ ጥረትም ሚዲያው ከመረጃ አቅራቢነት ባለፈ የከተማዋን ህዝብ የመዝናኛ ፍላጎት ከማሟላት አንጻር አይተኬ ሚና አለው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅትና ትብብር አጠናክሮ ቀጥሏል። ከሰሞኑ “ቡቤ” የተሰኘ ሲትኮም ድራማ ለማስጀመር ከጃንኮ ፕሮዳክሽን ጋር ያደረው የሥራ ስምምነት ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ በፊርማ ስነ ስርዓቱ ላይ፣ “ተቋሙ የትውልዱን ፍላጎት የሚያሟሉ ይዘቶች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ነው፡፡ አሁን ላይ እያደገ የመጣውን የመዝናኛ ኢንዱስትሪ ፍላጎት



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ‘ቡቤ’ የተሰኘ ድራማ ለማስጀመር የስራ ስምምነት ተፈራርሟል

ለማሟላት በኪነ-ጥበብ ዘርፍ ላይም ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዋና ስራ አስፈጻሚው ሁለተኛውን ኤኤምኤን ፕላስ ቻናል ካቋቋምን በኋላ የህዝባችንን የሚዲያ ጥማት ደረጃ በደረጃ እያረካን ነው ሲሉም አስረድተዋል፡፡

አቶ ካሳሁን አዲስ አበባ ለኪነ-ጥበብ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የቴአትር ቤቶችንና የኪነ-ጥበብ ማቅረቢያ አደባባዮችን እያሰፋች መሆኑን ጠቅሰው፣ ጥበባዊ ይዘቶችን ማምረት ደግሞ የአርቲስቶችና የሚዲያ ተቋማት ድርሻ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ከጃንኮ ፕሮዳክሽን ጋር የተደረገው ስምምነት የተመልካቾችን ፍላጎት የሚያሟላና የወጣቶችን ጥያቄ የሚመልስ በመሆኑ፣ የከተማነት ገጽታን የሚያንፀባርቁ ይዘቶችን ለተመልካች ለማድረስ ትልቅ ዕድል እንደሚፈጥር አንስተዋል፡፡

አቶ ካሳሁን አክለውም፣ “አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በየጊዜው መሻሻል እያሳየ፣ አመርቂ ውጤትም እያመጣ የሚገኝ ሜትሮፖሊታን ሚዲያ ነው፡፡ ‘ተወዳዳሪ ሚዲያ እንሆናለን’ ስንልም ዋነኛ ተልኳችን በይዘት፣ በአቀራረብ፣ በቴክኖሎጂ እና በሰው ሃይል ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ብዙ ነገር እየተሰራ ነው” በማለት አስረድተዋል፡፡

“አዲስ አበባ ሁሉን አቀፍ እድገት እና ለውጥ እያሳየች ትገኛለች፡፡ ይህ ለውጥና እድገት ደግሞ በመዝናኛው፣ በትምርትና በሌሎችም መንገዶች ማህበረሰቡ ጋር መድረስ አለበት፡፡ እናም ‘ለማህበረሰቡ ድምጽ እንሆናለን፣ እያዝናናን፣ እናስተምራለን’ ስንል በንድፈ ሃሳብ ብቻም ሳይሆን በተጨባጭ ተግባራትና በስራዎቻችን ነው” ሲሉም አክለዋል፡፡

ይህ የዋና ስራ አስፈጻሚው ሃሳብ አንድሬ ገብርኤል ኒኮላ የተባሉ የዘርፉ ባለሙያ በሰሩት ጥናትም የተረጋገጠ ነው፡፡ አጥኚው “Popular Media as Entertainment-Education” በሚል ርእስ እ.ኤ.አ. በ2025 በሳተሙት ጥናት አንድ ሚዲያ አሳታፊ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ማህበረሰቡን በማዝናናት፣ በማስተማር እና በማወያየት ለእድገትና ለሁሉን አቀፍ ለውጥ የማነሳሳት ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ ሲሆን በአንድ ሀገርና ከተማ ለውጥና እድገት እውን እንደሚሆን በጥናታቸው ጠቅሰዋል፡፡

የጃንኮ ፕሮዳክሽን መስራች ዋቆ ጌታቸው በበኩላቸው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከአዲስ አበባ ለውጥ ጋር አብሮ የሚራመድ ሚዲያ መሆኑንና አብሮ ለመስራት በመወሰናቸው መደሰታቸውን ገልጸዋል። “ቡቤ” የተሰኘው አዲስ የኮሜዲ ሲትኮም በኤኤምኤን ፕላስ ሲቀርብ ለይዘትና ለጥራት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራም አረጋግጠዋል።

ድራማው እያዝናና የሚያስተምር እና በከተማ ያለውን ማህበራዊ መስተጋብር የሚያንጸባርቅ እንደሆነ የተናገሩት ዋቆ ጌታቸው፣ ከፕሮዳክሽን ጥራት አንጻር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ያለው የቴክኖሎጂ አቅም አብሮ ለመስራት የሚያስችል ነው። ጊዜው የዲጂታል ዘመን እንደመሆኑ ከኤኤምኤን ፕላስ በተጨማሪ በዲጅታል ሚዲያም እንደሚለቀቅ አብራርተዋል፡፡

በእርግጥም በአንድ ግዙፍ ሜትሮፖሊታን ከተማ ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብ ፍላጎት ዘርፈ ብዙ ነው። ነዋሪው መረጃን ብቻ ሳይሆን፣ ማንነቱን የሚገልጽ፣ የዕለት ተዕለት ውጥረቱን የሚያቃልልና የተስፋ ስንቅ የሚሆነው መዝናኛ ይሻል። አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ (AMN) ይህንን የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት በመረዳት፣ ራሱን የ“የትውልድ ድምፅ” እና የ“ሜትሮፖሊታን ሚዲያ” ተምሳሌት አድርጎ እየገነባ ይገኛል፡፡

የሜትሮፖሊታን ሚዲያነት መገለጫው ዘመናዊነት፣ ተደራሽነትና ጥራት ነው። ተቋሙ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የከተማዋን ወጣቶችና ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳትፉ ፕሮግራሞችን ቀርጾ ወደ ስራ ገብቷል። ይህ እንቅስቃሴ ደግሞ በሚዲያና በመዝናኛ ኢንዱስትሪው፣ በሚዲያውና በመዲናዋ ነዋሪዎች መካከል አዲስ ድልድይ እየገነባ ይገኛል።

ሚዲያው ለከተማዋ የጥበብ እድገት ካበረከታቸው ትላልቅ ስራዎች መካከል “አዲስ ታለንት ሾው” አንዱ ነው። ይህ ፕሮግራም መድረክ አጥተው ለነበሩ በርካታ ወጣት የጥበብ ባለሙያዎች ትልቅ በር የከፈተ ነበር። የ“አዲስ ታለንት ሾው” ስኬት ለተቋሙ መነቃቃትን ፈጥሮ፣ አሁን ደግሞ “ውብ አዲስ” የተሰኘ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ለህዝብ ለማድረስ በዝግጅት ላይ ይገኛል። “ቡቤ” ደግሞ ተጨማሪ የመዝናኛ አማራጭ ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡ ይህም ተቋሙ ለከተማዋ እድገትና የነዋሪዎቿን የመዝናኛ ፍላጎት ለማሟላት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ተግባር ነው፡፡

## ማስታወቂያ

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 514 በወ/ሮ የኔነሽ በቀለ ተሰማ ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር AA000020500430 ሴሪ ቁጥር L 003378 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 18/06/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 09 ቀበሌ 07 በአዲሱ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 658 በወ/ሮ ወርቅነሽ ወታንጎ ህማ ስም የወጣው ቁጥሩ አ/06/02/3766 ሴሪ ቁጥር 113647 በቀን 23/07/2001 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ኦርጂናል ካርታ ስለጠፋባቸው በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 17/06/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ሙሉጌታ አየለ ድሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 5 መለያ ቁጥር AA000061007382389004 የሆነው ሰርተፍኬት በቅ/ፅ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ካርታ ሴሪ ቁጥር 0324933 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቸዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቅያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ/ እንደምሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ጊዜውን የዋጀው የአካዳሚው ስልጠና

- **አካዳሚው የሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ቴክኖሎጂን ማዕከል ያደረጉ በመሆናቸው የተቋማትን የማስፈጸም አቅም እያሻሻሉ መሆኑ ተጠቁሟል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ

ADDIS ABABA LEADERSHIP ACADEMY

በአሁኑ ወቅት የአንድ ሀገር ዕድገት የሚለካው ባለው የተፈጥሮ ሀብት ብቻ ሳይሆን፣ ያንን ሀብት በዕውቀትና በቴክኖሎጂ ወደ ላቀ እሴት የሚቀይር የሠለጠነ የሰው ኃይል በመገንባቱ ጭምር ነው። በዚህ ረገድ አካዳሚዎች ለመንግሥትና ለግል ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች የሚሰጡት ሥልጠና፣ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የማማከር አገልግሎት የሀገርን የማስፈጸም አቅም በመገንባት ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው።

አካዳሚዎች የሚሰጡት ሥልጠና ውጤታማ እንዲሆን ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎችን (እንደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ቢግ ዳታ እና ክላውድ ኮምፒውቲንግ) በከፍተኛ ደረጃ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ቴክኖሎጂው እንደ ተጨማሪ ግብዓት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ዋና የማስተማሪያና የጥናት መሣሪያ መወሰድ አለበት። ይህም አመራሮች በተግባር ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ውስብስብ ችግሮችን በዲጂታል መድረክ ተለማምደው ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላል። ሥልጠናዎች በግምት ሳይሆን፣ ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት አድርገው እንዲሰጡ በማድረግ ክፍተቶችን በውል ለመለየት ይረዳል።

ስለዚህ አካዳሚዎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በስፋት በመጠቀም ረገድ አርአያ መሆን ይገባቸዋል። ሠልጣኞችም በሥልጠና ቆይታቸው ሁሉንም አገልግሎቶች በዲጂታል መንገድ እንዲያገኙ በማድረግ፣ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ባህል በውስጣቸው እንዲሰርፅ ያደርጋሉ። ይህም ባለሙያው ወደ መደበኛ ሥራው ሲመለስ ያካበተውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክህሎት በተቋሙ ውስጥ እንዲተገብርና ለለውጥ ዝግጁ እንዲሆን ያነሳሳዋል። የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የተመሠረተውም ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

አካዳሚው በሠለጠነ የሰው ኃይል ለሥልጠና እና ምርምር አገልግሎት የሚውሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ለመንግሥትና ለግል ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች ክፍተትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና፣ ችግር ፈቺ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር፣ የማማከር እና የማኅበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የማጎልበት ዓላማ ይዞ ነው ወደ ሥራ የገባው። ለመሆኑ አካዳሚው በሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎችን በምን ልክ ይጠቀማል? በተቋማት ዘንድ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ባህል እንዲዳብር በማስቻል ረገድ ምን አስተዋፅኦ እያደረገ ነው? ከተማዋ የተያያዘችው አገልግሎትን የማዘመን ጥረት የላቀ ፍሬ እንዲያፈራ ምን ድጋፍ ያደርጋል? የሚሉ ነጥቦችን መፈተሽ ያስፈልጋል።

አዲስ አበባ የጀመረችው አገልግሎትን የማዘመንና 'ስማርት' የማድረግ ጥረት የላቀ ፍሬ እንዲያፈራ አካዳሚው የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ስለመሆኑ በአካዳሚው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የሲስተም አድሚኒስትሬተር ከፍተኛ ባለሙያ ወይዘሮ ጽዮን ተስፋዬ ተናግረዋል። አክለውም፣ አካዳሚው በሚሰጣቸው የጥናትና ምርምር፣ ሥልጠና፣ ማማከርና የማኅበረሰብ አገልግሎቶች ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ባህል እየዳበረ መጥቷል ብለዋል።

አካዳሚውን ሙሉ በሙሉ ከወረቀት ነፃ ሊያደርግ የሚችል የተቀናጀ ሲስተም (Integrated Resource Planning) ተብሎ የሚጠራ፣ ዐሥራ ሦስት ሞጁሎችን በአንድ የሚይዝ የኢ.አር.ፒ (ERP) ሲስተም እየተገነባ መሆኑን ገልጸው፣ ይህ የተቀናጀ ሲስተም በሙከራ ትግበራ ላይ እንደሚገኝና ወደ ተግባር ሲገባ በርካታ ክፍተቶችን እንደሚደፍን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የዲጂታል ሥልጠና መደላድል ከመዘጋጀቱም ሌላ ቪዲዮ ኮንፈረንስም ተግባራዊ ሆኗል ብለዋል። አካዳሚው ያለው የሰው ኃይልና የሥልጠና ክፍል ውስን በመሆኑ ሥልጠናዎችን በቪዲዮ ኮንፈረንስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መስጠት የሚያስችል ቴክኖሎጂን ከመጠቀሙም ሌላ ለጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚሆኑ የዌብ ሳይት፣ የኦርጋናይዜሽን ኢሜይል እና የተለያዩ ሶፍትዌሮች በቀላሉ በአካዳሚው እንዲገኙ መደረጉ ውጤት እያመጣ ነው ብለዋል።

የከተሞችን የትራፊክ ፍሰት፣ የቆሻሻ አወጋገድና የውኃ አቅርቦት ችግሮች በቴክኖሎጂ ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራዊ ጥናቶችን ማቅረብ ከአካዳሚዎች ይጠበቃል። የከተማ አመራሮች ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ፣ ለዘመናዊ አሠራሮች በጀትና ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግም ተጨማሪ ኃላፊነታቸው ይሆናል። እንደ መታወቂያና የንግድ ፈቃድ ያሉ የሕዝብ አገልግሎቶች በኦንላይን እንዲሰጡ የሚያስችል የክህሎት ሥልጠና ለባለሙያዎች መስጠትም ከአካዳሚው ይጠበቃል። አካዳሚዎች የዕውቀት ማዕከል ብቻ ሳይሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ድልድዮችም ናቸው። የሚሰጡት ሥልጠና ከንድፈ-ሀሳብ ባለፈ ቴክኖሎጂን ማዕከል ያደረገ ሲሆን፣ የከተሞችን ብልጽግና ማረጋገጥና የተቋማትን የማስፈጸም አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ይቻላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ ሥልጠናዎችን ተደራሽ ለማድረግ የዲጂታል መድረኮችን በመጠቀም ላይ መሆኑን ከአካዳሚው የተገኘው መረጃ ያሳያል። በተለይ በቪዲዮ ኮንፈረንስ የውጭ ሀገርና የሩቅ አካባቢ ምሁራንን በቀጥታ ስርጭት በማገናኘት ልምድ እንዲያካፍሉ የሚያደርግበት ዘዴ ተጠቃሽ ነው። በዲጂታል ሞጁሎችም ሠልጣኞች በፈለጉት ቦታና ጊዜ የትምህርት ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ በኦንላይን የመረጃ ልውውጥ የመጠቀም ሥራም አጠናክሮ ይዟል።

የአስተዳደር ሥራዎችን በማዘመን ተቋማዊ ቅልጥፍናን ለመጨመር የዲጂታል መሣሪያዎችን ተግባራዊ እያደረገ መገኘቱም ሌላው ጥንካሬው ነው። በተለይ በመረጃ አያያዝ ረገድ የሠልጣኞችን መረጃ፣ ውጤት እና ሰርተፊኬት በዲጂታል መንገድ በማደራጀት የወረቀት ሥራን መቀነስ መቻሉ ይበል የሚያሰኝ ጅምር ነው። በተረፈ የምርምርና ሕትመት ሥራዎችን በዲጂታል ላይብረሪ ለማካተት የጀመረው ተግባር መልካም ሥራ ነው። ሠልጣኞችና ተመራማሪዎች ዓለም አቀፍ የጥናት ውጤቶችንና መጻሕፍትን በቀላሉ የሚያገኙበትን የኢንተርኔት መሠረተ ልማት ማጠናከር ይህን ሥራ ከዳር ለማድረስ ያስችላል።

አካዳሚው አገልግሎቱን ይበልጥ ግልጽና ተደራሽ ለማድረግም፣ በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ አካባቢ በየወረዳውና በየክፍለ ከተማው ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ይሰጥ ዘንድ ጥናት ማድረጉ እገዛ አድርጓል ያሉት ወይዘሮ ጽዮን፣ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት ሥልጠና በምን መልኩ ቢሰጥ ይሻላል? የሚለውን መዳሰስ መቻሉን አስረድተዋል።

ለጥናቱ እንደ ዋና መነሻ የሆነውም አመራሮች በሥራ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ተቋሙ ሥልጠና ለመስጠት መቸገሩና አመራሩንም ሆነ ባለሙያውን የማብቃት ኃላፊነት የተሰጠውም ራሱ ተቋሙ በመሆኑ፣ በምን መልክ ሥልጠና ቢሰጥ ይሻላል? በሚለው ጉዳይ ላይ ጥናት ተደርጎ የአብዛኛው ምላሽ "በኦንላይን ቢሰጥ በምንፈልገውና በሚያመቸን ቦታና ጊዜ መሰልጠን እንችላለን" የሚል እንደነበር ተናግረዋል።

በተለይ በቅርብ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች አብዛኞቹ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ ናቸው። የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በዋናነት ኃላፊነት የተሰጠው ደግሞ ሰውን ማብቃት ላይ ነው። ቴክኖሎጂዎች በየተቋማቱ ተተግብረዋል፤ የተተገበሩ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀመውም በየተቋማቱ ያለው የሰው ኃይል በመሆኑ እየሠራን ያለነው እሱ ላይ ነው ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ጽዮን ማብራሪያ፣ በወረዳም ሆነ በክፍለ ከተማ ደረጃ ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ቴክኖሎጂን መተግበር የሚችሉ እንዲሆኑ "ዲጂታል ሊደርሺፕ" የሚባል የሥልጠና ሞጁል ተዘጋጅቶ ሥልጠናው ተጀምሯል። ተቋሙ ከጥናትና ምርምር ሥራዎቹ ጎን ለጎን ችግሮችን በመፈተሽ ያሉበትን ደረጃ ካወቀ በኋላ ለተቋማት የምክረ ሐሳብም ይሰጣል። በዚህ መሠረትም ተከታትሎ ያሉበትን ደረጃ ለሚመለከተው አካል በሪፖርት ያሳውቃል።

ወረዳዎች እና ክፍለ ከተሞች ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች ብሎም ከሴክተር ተቋማት መረጃን በቴክኖሎጂ እንዲሰበስቡ እየተደረገ ነው ብለዋል። የተቋማት አገልጋዮች ከቴክኖሎጂ ጋር የተላመዱ ናቸው ወይስ አይደሉም? በወረቀት ነው ወይስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ነው የተሻለ መልስ የሚሰጡት? የሚለውን እንዲሁም ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ከመፍራት ጋር ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት ተሞክሯል ብለዋል።

በዚህ ረገድ ውስንነቶች ቢኖሩም ሰዎች በሥልካቸው ጭምር ቴክኖሎጂውን የትም ቦታ ሆነው እንዲጠቀሙና እንዲላመዱ ለማድረግ እየተሞከረ ሲሆን፣ እስከ አሁን ባለው ሂደት ጥሩ እንቅስቃሴ እንዳለ ገልጸዋል።

ሆኖም ግን ቴክኖሎጂውን የሚጠቀመው ማኅበረሰቡ ብሎም የግልና የመንግሥት ተቋማት ስለሆኑ ይህን ተገንዝቦ በፍጥነት ግንዛቤ ፈጥሮ መተግበር ያስፈልጋል ያሉት ወይዘሮ ጽዮን፣ አካዳሚው ደግሞ ይህን ተልዕኮ ለመፈጸም ትልቅ ሚና ስላለው ባለው ላብራቶሪ አዳዲስ የተተገበሩ ቴክኖሎጂዎችን ጭምር በማካተት እየሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። የተለያዩ ተቋማት ከአካዳሚው መነሻ ተደርጎ አልያም በፍላጎት እየመጡ ቴክኖሎጂዎችን እንደሚለማመዱም ጠቁመዋል።

በከተማዋ በርካታ ቴክኖሎጂዎች ቢተገበሩም የአጠቃቀም ውስንነቶች አሉ፤ በተለይ የማኅበረሰቡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ባህልና ዕውቀት አለመዳበር፣ ተቋማትም የተጀመሩ ቴክኖሎጂዎችን ከማስቀጠል ጋር ተያይዞ ችግሮች አሉ ባይ ናቸው። በተጨማሪም ሥራዎች ከላይ ጀምሮ የተቀናጁ (Integrated) አለመሆን ስለሚስተዋልባቸው፣ እሱን አቀናጅቶ መተግበርና ግቡን እንዲመታ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አክለዋል፡፡

አሁንም በተለመደው አሠራር ለመቀጠል እግር መጎተትና አዳዲስ ሙከራዎችን ፈጥኖ አለመቀላቀል ይስተዋላል ብለው፣ ለአብነትም ሰው ሠራሽ አስተውሎትን (AI) ለመግፋት የሚደረግ ሙከራ አለ፤ ይህ ቴክኖሎጂ በርካታ ጥቅሞች አሉት፤ በተለይ የአመራር ውሳኔዎችን ለመደገፍ የዳታ ትንተና ሥራዎችን በላቀ ሁኔታ የመጠቀምን ዕድል ከመስጠት አንፃር የላቀ እገዛ ያበረክታል።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውጤታማ የሚሆነው የአመራሩን የአስተሳሰብ ለውጥ ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ማጣጣም ሲቻል ብቻ እንደመሆኑ በተጠናከረ የግንዛቤ ሥራ የአስተሳሰብ ልዕልና ማምጣት ማስፈለጉ ነው፡፡

# ልጆች፤ ስለ ዓድዋ ድል ታሪክ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ፎቶ- ከፋይል
ልጆች የዓድዋ ድል መታሰቢያን ሲጎበኙ

ሰላም ልጆች! ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ጥሩ ነው እንደምትሉ እርግጠኛ ነን። በዚህ ሳምንት ያዘጋጀንላችሁ ጽሑፍ የዓድዋን ድል የሚመለከት ነው፡፡ ለመሆኑ ስለዚህ ታሪክ ምን ያህል ታውቃላችሁ? ሀሳባችሁን ከቤተሰቦቻችሁ አልያም ከጓደኞቻችሁ ጋር ተለዋወጡ፡፡ ለመነሻ ይሆንላችሁ ዘንድ የሚከተለውን ጽሑፍ አዘጋጅተንላችኋል፡፡ ስለ ድሉ መረጃ የሚያጋሯችሁ እንግዳ ራሳቸውን በማስተዋወቅ ማብራሪያ ይሰጧችኋል፤ በተመስጦ እንድታነቡ ጋበዝናችሁ፡፡

ልጆች እንዴት ናችሁ? አባት አርበኛ መኮንን መሸሻ እባላለሁ፡፡ የዓድዋ ጦርነት የካቲት 23 ቀን 1888 ዓመተ ምህረት በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል የተካሄደ ነው፡፡ ይህ ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት ዓድዋ በሚባል አካባቢ ተጠናቋል፡፡ የዓድዋ ድል የተባለውም ለዚሁ ነው፡፡ ይህ ድል የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ትግል ውጤት ተደርጎም በዓለም ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ ሊወራት የመጣውን ጣሊያንን እንድታሸንፍ የረዳት፣ በጦርነቱ ወቅት ኢትዮጵያውያን በብሔርና በኃይማኖት ሳይከፋፈሉ፣ ሴት ወንድ ሳይሉ በአንድነታቸው ቆመው መዋጋታቸው ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በሀገራችን ጉዳይ ላይ በጋራ መቆም ለአሸናፊነት እንደሚያበቃ ነው፡፡


በዓድዋ ጦርነት ወቅት ጣሊያኖች ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቀው ሊወጉን ቢመጡም፣ ኢትዮጵያውያን በአግባቡ ተደራጅተንና በአንድነት ቆመን ማሸነፍ ችለናል፡፡ በጦርነቱ ሴቶች በመዋጋትና በማዋጋት፣ ለራበውና ለጠማው ውሃና ምግብ በማቅረብ፣ የተመታውን ደሙን ባላቸው ጨርቅ እያሰሩ፣ እንዲሁም “በርታ ወደ ኋላ እንዳትል” እያሉ ሠራዊቱን በመደገፍ ታሪክ ሠርተዋል፡፡

ልጆች፤ በዓድዋ ጦርነት ወቅት 12 የጦር መሪዎች ነበሩ፡፡ እነዚህም መሪዎች፡- ፊታውራሪ ገበየሁ ገቦ ጉርሙ፣ ልዑል ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተሰማ ጎሹ፣ ንጉሥ ሚካኤል አሊ ሊበን፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ ሮባ፣ ራስ ወሌ ብጡል ኃይለ ማርያም፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ ሁንዱል፣ ራስ አሉላ እንግዳ ቁቢ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ምርጫ፣ ዋግሹም ጓንጉል ብሩ ገብረ መድህን፣ ራስ አባተ ቧያለው ንጉሡ እና ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ቢተርፉ ናቸው፡፡

ልጆች፤ ኢትዮጵያ የሰው ሀገር አትፈልግም፣ ራሷንም አታስደፍርም፤ ሲነኳትም አትወድም፡፡ በዚህም መሠረት በቅኝ ግዛት ያልተያዘች ሀገር ናት፡፡ እናንተም ለሀገራችሁ ትምህርታችሁን በርትታችሁ በመማር እና ከእናንተ የሚጠበቀውን በማድረግ ሀገራችሁን በዓለም ማስጠራት አለባችሁ፡፡

ልጆች፤ ስለ ድሉ የነገርኳችሁ በጥቂቱ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ፍቅር በአንድነት ወራሪውን የጣሊያን ጦር ድል ያደረጉበት፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች ስለ ነፃነታቸውና ስለአንድነታቸው በጋራ መቆም እንዲችሉ ያስቻለው ድል 130ኛው ዓመት ዘንድሮ ይከበራል፡፡ መልካም በዓል ይሁንላችሁ፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ጉድ መጣ ጉድ መጣ ከመሬት ውስጥ ልቃቂት ወጣ**

**መልስ፡-** ሐ. ነጭ ሽንኩርት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**በሦስት እግሩ ቆሞ የሚፈነጥዝ**

ሀ. ሽማግሌ
ለ. ወጥ
ሐ. ካንጋሮ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ፋና ወጊው አገልግሎት አሰጣጥ

በደረጀ ታደሰ

በአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመንና ብልሹ አሠራሮችን ለማስቀረት የተቋቋመው አዲስ መሶብ "የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት፣ ወደ ሥራ ከገባ ጥቂት ወራትን አስቆጥሯል። ተቋሙ የወረቀት ንክኪን ያስቀረ፣ ጉዳይ አስፈፃሚን (ደላላን) ከጨዋታ ውጭ ያደረገ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎትን ያቀረበ፣ ግልጽነት የሰፈነበት አሠራር የዘረጋ ስለመሆኑ እየተመሰከረለት ይገኛል፡፡

አሁን ያለንበት የየካቲት ወር የዓድዋ ድል በዓል የሚከበርበት ነው፡፡ የዓድዋ ድል፣ ጠላትን በጦር ሜዳ ከማሸነፍ የላቀ ትርጉም ያለው ነው፡፡ ድሉ ድንበር የሚሻገር፣ ከትውልድ ትውልድ በክብር የሚወረስ፣ ለአገር እና ለሕዝብ የሚከፈል መስዋዕትነት እስከ ምን ድረስ እንደሆነ የሚገለጥበት ነው፡፡ ይህንን ታላቅ ድል መነሻ በማድረግ፣ እንደ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት አገልግሎትን በላቀ ደረጃ እያቀረበ በሚገኘው የአዲስ መሶብ እያገለገሉ ያሉ ባለሙያዎችን የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል አነጋግሯቸዋል፡፡ እነሱም በተቋሙ እየተገነባ ስላለው የሥራ ባህልና ስለ ዜግነት ድርሻቸው የሚከተለውን ብለዋል፡፡

## ከእኛ የሚጠበቀው በዲጂታል ቴክኖሎጂ አገርን በማሳደግና ሕዝብን በሙያ በማገልገል ታላቅነትን ማረጋገጥ ነው

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት የነዋሪነት መታወቂያ ለማውጣት በሄድኩበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ካጋጠመኝ እንግልት 'መንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጥሬ አልሠራም' የሚል ውሳኔ ላይ አድርሶኝ ነበር፡፡ ሆኖም አዲስ መሶብን ካሰብኩት በላይ ዘመናዊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ተቋሙ ከሕንፃው ጀምሮ፣ አደረጃጀቱ፣ ግብዓቱና የሰው ኃይል አስተዳደሩ በጣም ዘመናዊ ነው፡፡ በሥራ ላይ ሕዝብን በክብር ማገልገልና ከተገልጋዮች አዎንታዊ ግብረ-መልስ ማግኘት የሚሰጠው የመንፈስ እርካታ ሥራዬን ይበልጥ እንድወደው አድርጎኛል፡፡ በዚህም ባለፉት ጥቂት ወራት ያሳለፍኩት ጊዜ በስኬት የተሞላ ነው፡፡

ተገልጋዮች በተለያዩ ስሜቶች (ቁጣ፣ መረበሽ ወይም ብስጭት) ተውጠው ሊመጡ ይችላሉ፤ አገልጋዮች ግን


አማኑኤል ዮሴፍ

ስሜታቸውን ተረድተው፣ አረጋግተው፣ አገልግሎት ሰጥተውና ደስተኛ ሆነው እንዲመለሱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። የቀድሞ አባቶቻችን በጦር ሜዳ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል፤ ከእኛ የሚጠበቀው ደግሞ በዲጂታል ቴክኖሎጂ አገርን በማሳደግና ሕዝብን በሙያ በማገልገል ታላቅነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

## ተገልጋዮችን የምንቀበላቸው በጥሩ ፈገግታና በእውነተኛ የአገልጋይነት ስሜት ነው

እኛ እዚህ የምንሰጠው አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘ ነው፡፡ አገልግሎቱ ከወረቀትና ከእጅ ንክኪ ውጭ መሆኑ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ተገልጋዮች ወደ ተቋሙ ሲመጡ የምንቀበላቸው በጥሩ ፈገግታና በእውነተኛ የአገልጋይነት ስሜት ነው። ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸውን ሰነዶች በሶፍት ኮፒ በተቀየረ አግባብ ማሟላታቸውን አረጋግጠን እናስተናግዳቸዋለን፡፡

ቀደም ሲል በሌላ የመንግሥት ተቋም እሠራ ነበር፡፡ ያኔ ዲጂታል ቴክኖሎጂው ከማንዋል አሠራር ጋር ተቀላቅሎ ይሠራ፣ የወረቀት ፋይሎችም ቢሮውን ያጨናንቁት ነበር፡፡ ፋይሉን ለማደራጀት እና ፈልጎ ለማውጣት ጊዜና ጉልበት ይወስድ ነበር፡፡ ይህም አገልግሎቱን ያጓትታል፣ ተገልጋዩንም ለእንግልትና ለምሬት ይዳርጋል፡፡ አሁን በአዲስ መሶብ ውስጥ ይህ ሁኔታ የለም።

ሌላው አዲስ መሶብ ያስቀረው ብልሹ አሠራር የደላሎች ጣልቃ ገብነትን ነው፡፡


ኬመርት አለማየሁ

በአዲስ መሶብ አገልግሎት የሚሰጠው በአካል ወይም በተወካይ ብቻ ነው፡፡ በጉዳይ አስፈጻሚዎች (ደላሎች) የሚከናወን ምንም ዓይነት ሥራ የለም፡፡ ይህ አሠራር ለሙስና ፈጽሞ ክፍተት አይሰጥም፡፡

አሰራሩ ፋይል አልተገኘም፣ ኃላፊ የለም፣ ስብሰባ ነን የሚሉ ሰበቦች በአዲስ መሶብ ተቀባይነት የሌላቸውና የማይታወቁ ናቸው። እንደ አንድ ኢትዮጵያዊት በዚህ ተቋም ማገልገሌ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል። የየካቲት ወር የዓድዋ ድል የሚከበርበት በመሆኑ ትውልዱ ጦር ሜዳ ሳይዘምት ዕውቀቱንና ጊዜውን ለአገር ልማት በማዋል የጀግኖች አባቶችን አደራ ሊወጣ ይገባል።

ፎቶ- ከፋይል


ቅድስት ክፍሌ

## ሌብነትና ብልሹ አሠራር የማይሞከሩ 'ቀይ መስመሮች' ናቸው

ተቋሙ ሲመሰረት ዓላማው የመንግሥት አገልግሎቶችን ዘመናዊ፣ ፈጣን፣ ፍትሐዊና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህም ቢሮዎች በቴክኖሎጂ የተሟሉና ለሥራ ምቹ ሆነው ተደራጅተዋል።

እኔ እዚህ ከመምጣቴ በፊት በንግድ ቢሮ ሠራኛ ነበርኩ። በተቋሙ የኦንላይን አገልግሎት ከሁለት ዓመት በፊት የተጀመረ ቢሆንም፤ የኔትወርክ እና የኃይል መቆራረጥ፣ የሰነዶች ወደ ሶፍትኮፒ አለመቀየርና አለመደራጀት ምክንያት አገልግሎቱን ሙሉ ለሙሉ ዲጂታል ማድረግ አልተቻለም። ይህም የተገልጋይን እንግልትና ቅሬታ በሚፈለገው ልክ እንዳይቀንስ አድርጓል።

የአዲስ መሶብ ግን ለተገልጋይም ለአገልጋይም ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ተገልጋይ ያለ አድሎ የሚፈልገውን አገልግሎት ያገኛል። የኔትወርክና የኃይል መቆራረጥ የለም፡፡ እኔ ተቋሙ አገልግሎት ከጀመረበት ቀን አንስቶ በሥራ ላይ ነኝ። አንድም ቀን ከሲስተም መቆራረጥ ጋር የተያያዘ ችግር አላጋጠመንም። ችግር እንኳን ቢፈጠር ፈጣን ምላሽ የሚሰጡ ባለሙያዎች ነቅተው ይጠብቃሉ፡፡ ሠራተኛው በሥራ ስነ ምግባር የታነፀ ነው፡፡

የአዲስ መሶብ ሠራተኞች ወደ ተቋሙ የሚቀላቀሉት በብዙ መመዘኛዎች ተለይተውና ጥብቅ ስልጠናዎችን ወስደው ነው፡፡ ሌብነትና ብልሹ አሠራር የማይሞከሩ ቀይ መስመሮች ናቸው። ሠራተኛው በሥራ ሰዓት የግል ስልክ መጠቀም አይፈቀድለትም። ይህ የሥራ ሰዓት ለሥራ ብቻ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በዓድዋ ድል አባቶቻችን ነፃ አገር አስረክበውናል። የእኛ ትውልድ ደግሞ አገራችን ከሌሎች ጋር እንድትወዳደር የሚያስችላትን ኢኮኖሚያዊ አቅምና ቴክኖሎጂ የመገንባት ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ረገድ እኔም የዜግነት ድርሻዬን ለመወጣት ቃል እገባለሁ፡፡


አናቶሊ ገመቹ

## ስለ መንግሥት ተቋማት የነበረኝን አሉታዊ አመለካከት በተግባር ቀይሬያለሁ

ወደ አዲስ መሶብ የተቀላቀልኩት ከዩኒቨርሲቲ እንደተመረቅኩ ነው፡፡ ቀደም ሲል ስለ መንግሥት ተቋማት አገልግሎት የነበረኝ ግንዛቤ በጣም አሉታዊ ነበር፡፡ የሕዝብ ምሬትና የኋላ ቀር አሠራር ምንጭ እንደሆኑ አስብ ነበር፡፡ ነገር ግን እዚህ መጥቼ ያገኘሁት የሥራ ከባቢና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አመለካከቴን ሙሉ በሙሉ ቀይሮታል፡፡

ተገልጋዮች ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ከፍለው እንደሚመጡ በመረዳት፣ እነሱን ማክበርና ማገልገል እንደ ትልቅ ክብር እንቆጥረዋለን፡፡ እንደ አመጣጣቸው በትህትና እንቀበላቸዋለን፡፡ የሚፈልጉትን አገልግሎት በፍጥነትና ከአድልዎ ነፃ በሆነ መንገድ ለመስጠት ጥረት እናደርጋለን፡፡

አዲስ መሶብ በወራት ዕድሜ ውስጥ አበረታች ውጤት እያሳየ ነው። ይህንን ለማስቀጠል ኃላፊነቴን በብቃት መወጣቴን እቀጥላለሁ፡፡ ተወዳዳሪ የሆነ የዲጂታል አገልግሎት ለማስፋፋት እንደ ወጣትነቴ፤ በተቋሙ ውስጥ ካለው ወጣት የሠው ኃይል ጋር በመተባበር ከዚህ የተሻለ ውጤት እንዲመጣ በትጋት እሠራለሁ። ይህንን የሥራ ባህል እንድናዳብር ሥራ ከመጀመራችበን በፊት የተሠጠን ስልጠና ትልቅ እገዛ አድርጎልናል፡፡

የዓድዋ ድልን ስኬት በተግባር ለመድገም እና በዲጂታል ዘመን ውስጥ ተወዳዳሪ የሆነ አገልግሎት ለማስፋፋት ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን በትጋት ለመስራት ተነሳስቻለሁ፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የበጋ መስኖ ምርታማነትን ለማሳደግ ምን እየተሰራ ነው?

**በይግለጡ ጓዴ**



ፎቶ ከፋይል

በአዲስ አበባ ከተማ በበጋ መስኖ ልማት እየለሙ ከሚገኙ የአትክልት ምርቶች በጥቂቱ

በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ እየታየ ያለው ፈጣን የከተሞች ዕድገትና የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የከተማ ግብርናንና ዘመናዊ የመስኖ ልማትን ከአማራጭነት ባለፈ ለህልውና ወሳኝ ወደሆነ የስትራቴጂክ ምርጫ ቀይሮታል። እንደ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብና እርሻ ድርጅት (ፋኦ) መረጃ ከሆነ፣ በዓለም ዙሪያ ከ800 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በከተማ ግብርና ላይ የተሰማሩ ሲሆን፣ ይህም የከተማ ነዋሪዎችን የምግብ ፍላጎት ከማሟላት ባለፈ በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚከሰቱ የምግብ ዋስትና ስጋቶችን ለመቋቋም ትልቅ አቅም እየፈጠረ ይገኛል። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚከናወን የመስኖ ልማትም፣ ውስን የሆነውን የከተማ መሬትና የውሃ ሀብት በቁጠባና በብቃት በመጠቀም ከፍተኛ ምርት ለማግኘት የሚያስችል ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል።

እንደ ሲንጋፖር እና ኔዘርላንድስ ያሉ ሀገራት የመሬት ጥበትን ተቋቁመው በዘመናዊ መስኖ የታገዘ የከተማ ግብርናን ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋግረዋል። ለምሳሌ ሲንጋፖር የህንፃ ወለሎች እና ግድግዳ ላይ ግብርና (Vertical Farming) በከፍተኛ ደረጃ በማስፋፋትና የውሃ ፍጆታን በ90 በመቶ የሚቀንስ የሃይድሮፖኒክስ መስኖ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በምግብ ራሷን ለመቻል ግዙፍ ኢንቨስትመንት እያከናወነች ትገኛለች። በተመሳሳይ በኩባ ዋና ከተማ ሃቫና፣ የተለያዩ የከተማ ግብርና ስልቶችን በመጠቀም የከተማዋን 90 በመቶ የአትክልት ፍላጎት በውስጥ ምርት መሸፈን መቻላቸው ለአዳጊ ሀገራት ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ተሞክሮ ነው።

እነዚህ ዓለም አቀፍ ልምዶች እንደሚያሳዩት፣ በመስኖ የታገዘ የከተማ ግብርና ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው አንጻር የምግብ አቅርቦት ሰንሰለቱን በማሳጠር የትራንስፖርት ወጪንና የምርት ብክነትን ከመቀነሱም በላይ፣ ለከተማ ወጣቶችና ሴቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። በተጨማሪም የከተማን ሙቀት በመቀነስና የአካባቢ ጥበቃን በማረጋገጥ በኩል ያለው ሚና የላቀ ሲሆን፣ ከተሞች የራሳቸውን ምግብ በራሳቸው በማምረት የኑሮ ውድነትንና የገበያ መዛባትን በዘላቂነት እንዲቋቋሙ የሚያስችል የኢኮኖሚ ምሰሶ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

የከተማ ግብርና በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማም በስፋት ይከናወናል። በበጋ ወቅት ጭምር የመስኖ ልማት ስራን በማከናወን በርካቶችን ተጠቃሚ እያደረገች ትገኛለች፡፡ በተለይም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ 'የሌማት ትሩፋት' ንቅናቄን ተከትሎ በከተማዋ ሰፋፊ ክፍት ቦታዎች፣ በወንዝ ዳርቻዎችና በቤት ጓሮዎች ላይ የሚከናወኑ የግብርና ስራዎች ተጨባጭ ውጤት እያሳዩ ይገኛሉ። ይህ እንቅስቃሴ ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ ከማድረግ ባለፈ፣ የምግብ አቅርቦት ሰንሰለቱን በራስ አቅም ለመተካት የተያዘ ትልቅ ግብ ነው።

የበጋ መስኖ በክፍለ ከተሞች በሚገኙ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየተመረተ ይገኛል። ይህም ከተማዋ የራሷን የፍጆታ ፍላጎት በከፊል እንድታሟላ ትልቅ አቅም ይፈጥራል። በተለይም የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በወንዝ ዳርቻዎች ለምሳሌ በአቃቂ ወንዝ ተፋሰስ ላይ በትኩረት እየተሰራ ሲሆን፣ እንደ ጎመን፣ ካሮት፣ ሽንኩርት እና ሰላጣ ያሉ ተፈላጊ ምርቶች በመስኖ እየለሙ ይገኛሉ።

ይህ የበጋ መስኖ ምርት በቀጥታ ከከተማዋ እርሻ ለነዋሪው ስለሚቀርብ፣ ከፍተኛ የትራንስፖርት ወጪንና የደላላ ጣልቃ ገብነትን በመቀነስ ረገድ የሚጫወተው ሚና የላቀ ነው። ይህም በከተማዋ ነዋሪ ላይ የተጫነውን የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል እንደ ቁልፍ መፍትሄ ተወስዷል። በተጨማሪ በርካታ ወጣቶችና ሴቶች በግብርና ማህበራት ተደራጅተው ገቢ እንዲያገኙ በማድረግ ሰፊ የስራ ዕድልን እየፈጠረ ይገኛል፡፡

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆኑት አቶ ጌቱ ዱንዳ፣ በመስኖ ልማት ህይወታቸውን ከሚመሩ አርሶ አደሮች መካከል አንዱ ናቸው። አቶ ጌቱ ለረጅም ጊዜ በዘርፉ ቢቆዩም፣ በቅርቡ በተደረገላቸው የተቀናጀ ድጋፍ ተጠቃሚነታቸው በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን ይናገራሉ። በአሁኑ ወቅት ሰላጣ፣ ጎመንና ዝኩኒ እያመረቱ ሲሆን፣ ለዚህም 50 ኪሎ ግራም ዩሪያ እና ሌሎች የግብዓት ድጋፎችን ተጠቅመዋል።

"ምርቴን ወደ ገበያ በማቅረብ የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት ረገድ የራሴን ድርሻ እየተወጣሁ ነው" የሚሉት አቶ ጌቱ፣ በመንግስት በኩል የሚደረግላቸው የሙያ ምክርና የግብዓት ድጋፍ ለስኬታቸው ትልቅ አቅም እንደሆናቸው ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡

በተመሳሳይ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የሚኖሩት ወይዘሮ ከበቡሽ ኪዳኔም የዘርፉ ተጠቃሚ ናቸው። ብሮኮሊ፣ ሰላጣ፣ ካሮትና ቆስጣ በማምረት ስኬታማ የሆኑት ወይዘሮዋ፣ ከወረዳና ክፍለ ከተማ ባለሙያዎች የውሃ መሳቢያ ፓምፕ፣ የጸረ-ተባይ መርጫ ቴክኖሎጂ እና የማዳበሪያ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ገልጸዋል።

"ከመስኖ ልማት በማገኘው ገቢ ልጆቼን እያስተዳደርኩ ነው" የሚሉት ወይዘሮ ከበቡሽ፣ በዓመት ከሦስት ጊዜ በላይ በማምረት ውጤታማ መሆን መቻላቸውን ይናገራሉ። የመንግስት የወንዝ ዳርቻዎችን በማልማቱ ንጹህ ውሃ ማግኘት መቻላቸው ለስራቸው ትልቅ እገዛ አድርጓል፡፡

የከተማ ግብርናው ለወጣቶችም ሰፊ የስራ በር ከፍቷል። በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የሚገኘው ወጣት በለጠ ቦጋለ በሁለት ሄክታር መሬት ላይ በመስኖ ልማት ተሰማርቶ ይገኛል። ወጣቱ እንደ ቲማቲም፣ ጎመንና ቆስጣ ያሉ ምርቶችን በማምረት በስሩ ለ13 ወጣቶች ጊዜያዊ የስራ እድል መፍጠር ችሏል። በለጠ ለልማቱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም ትራክተር፣ የውሃ ፓምፕ እና ከፍተኛ መጠን ያለው ማዳበሪያ ጥቅም ላይ አውሏል። "የገበያ ዋጋ መቀነስ ካላጋጠመን የተሻለ ገቢ እናገኛለን" የሚለው ወጣቱ፣ ሌሎች ወጣቶችም በከተማ ግብርና ላይ ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥሪውን ያቀርባል።

ሌላው የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ተጠቃሚ ወጣት ፍቅሩ ደሳለው፣ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በዘርፉ ተሰማርቶ ቲማቲም፣ ጎመንና ሽንኩርት በማምረት ላይ ይገኛል። ስራውን ከመውደዱ የተነሳ ቀድሞ ተቀጥሮ ሲሰራ ከቆየ በኋላ፣ አሁን ላይ ራሱን ችሎ መሬት በመከራየት ስራውን እያስፋፋ ይገኛል። ፍቅሩም በስሩ ለሦስት ሠራተኞች የስራ እድል መፍጠር የቻለ ሲሆን፣ የበጋ መስኖ በትኩረት ከተሰራበት የኢኮኖሚ አቅምን እንደሚገነባ በተግባር አሳይቷል።

በአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 9 የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የሆልቲካልቸር ባለሙያ አቶ ጠና ነገራ፣ በወረዳው በበጋ መስኖ 129 ሄክታር መሬት መልማቱንና 42 አርሶ አደሮች ተሳታፊ መሆናቸውን ይገልጻሉ። እንደ አቶ ጠና ገለጻ፣ በወረዳው ከበጋ መስኖ ልማት 4 ሺህ 161 ቶን ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። በተለይም በቲማቲም ልማት በሄክታር እስከ 500 ኩንታል ምርት በማግኘት ረገድ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየታዩ ነው።

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የእጽዋት ልማት ዘርፍ ቡድን መሪ አቶ ጉደታ ሽብሩ በበኩላቸው፣ በክፍለ ከተማው በ2018 የበጋ መስኖ 332 ሄክታር መሬት መልማቱን ጠቁመዋል። በልማቱ 224 አርሶ አደሮች(181 ወንድ እና 43 ሴት) ተሳታፊ ሲሆኑ፣ በዓመት በሦስት ዙር ከሚከናወነው ልማት 163 ሺህ 320 ኩንታል የአትክልት ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።አመራሩ ለመስክ ድጋፍ፣ ለቴክኖሎጅ አቅርቦት እና ለአፈር ማዳበሪያ ስርጭት ትኩረት በመስጠቱ ምርታማነቱ እየጨመረ መሆኑን አቶ ጉደታ አረጋግጠዋል፡፡

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማም በተመሳሳይ በ13 ወረዳዎች የወንዝ ዳርቻዎችን ተከትሎ የመስኖ ልማት እየተከናወነ ይገኛል። የክፍለ ከተማው የሆልቲካልቸር ባለሙያ ወይዘሮ መሰረት መካሻ እንደገለጹት፣ ለ525 ነዋሪዎች ዘጠኝ የውሃ መሳቢያ ፓምፖች፣ 600 ኩንታል ማዳበሪያ እና ልዩ ልዩ የዘር ግብዓቶች ድጋፍ ተደርጓል። ከዚህ ልማት 12 ሺህ 227 ቶን ምርት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም ነዋሪዎች ምግብን ከደጃቸው እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእጽዋት ሃብት ልማት ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ እንሴኔ፣ በከተማ ደረጃ በ2018 ዓ.ም በስድስት ክፍለ ከተሞች (ኮልፌ ቀራኒዮ፣ ንፋስ ስልክ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ቦሌ፣ ለሚ ኩራ እና ጉለሌ) እንቅስቃሴው በስፋት እየተተገበረ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ከተማ በበጋ መስኖ በአጠቃላይ 1 ሺህ 133 ሄክታር መሬት እየለማ ሲሆን፣ ከዚህም ከ46 ሺህ 160 ቶን በላይ የአትክልት ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።በልማቱ 1 ሺህ 899 ተጠቃሚዎች ተሳትፎ እያደረጉ ሲሆን፣ ለዚህ ስኬትም 7 በነዳጅ የሚሰሩ ፖምፖች፣ 61 በሶላር የሚሰሩ ፖምፖች፣ 79 የጸረ-ተባይ መርጫዎች እና 189 ኪሎ ግራም ልዩ ልዩ ዘሮች ጥቅም ላይ ውለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለው የበጋ መስኖ ልማት፣ ከተማዋን ከምግብ ጥገኝነት ወደ ራሷን መቻል የምታደርገው ሽግግር ማሳያ ነው። የምርት ገበያ ዋጋን ከማረጋጋት ባለፈ፣ ለወጣቶች የስራ እድል በመፍጠር እና የከተማዋን ገጽታ አረንጓዴ በማድረግ ረገድ ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው። የአመራሩ ቁርጠኝነት፣ የባለሙያዎች ድጋፍ እና የአርሶ አደሩ ትጋት ተቀናጅተው መቀጠላቸው፣ ከተማዋን በምግብ ዋስትና ራሷን የቻለች ተምሳሌት ያደርጋታል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# አሳሳቢው የድምፅ ብክለት እና መፍትሔው

- **በ2018 በጀት ዓመት በግማሽ ዓመቱ 5 ሺህ 780 በሚሆኑ ተቋማት ላይ የድምፅ ልኬት ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ተሰርቷል**

**በለይላ መሀመድ**

"ሲኤምሲ ሳህለተ ምህረት አደባባይ በርካታ የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴና ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ከሚታይባቸው አካባቢዎች አንዱ ነው። ከዚህ የተነሳ የመንገድ ላይ የተሽከርካሪዎች ድምፅ ብክለት ከፍተኛ ነው። ከመኪና የሚወጣው ድምፅ መጠን 86 ዲሲቢል ይደርሳል። በሰሚት 72 ለስላሳ ፋብሪካ አካባቢ የሚገኘው የብሎኬት ፋብሪካና የፕላስቲክ ፋብሪካ የሚወጣው ድምፅ በተመሳሳይ የድምፅ ብክለት ይፈጥራል። ለምሳሌ ፕላስቲክ መልሶ መጠቀም ላይ የተሰማራው ፋብሪካ የድምፅ መጠን 90 ዲሲቢል አካባቢ ደርሷል። የመኖሪያ አካባቢ ከመሆኑ አንጻር 55 ዲሲቢል መሆን የነበረበት ቢሆንም፣ በቅርቡ ከስታንዳርዱ በላይ ሆኗል" ሲሉ የድምፅ ብክለት በአዲስ አበባ ከተማ ሊያገኝ የሚገባውን ትኩረት ማሳያ የሆኑ አካባቢዎችን አንስተው ያብራሩት በአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለትና ተጽዕኖ ቡድን መሪ ወይዘሮ ሰናይት ተስፋ ናቸው።

ለመሆኑ የድምፅ ብክለት ምንድነው? እንዴት ይከሰታል? የሚያመጣው ቀውስ ምን ይመስላል? የሚለውን በውል በመገንዘብ ለመፍትሔው መረባረብ ያስፈልጋል። በተቋሙ የአካባቢ ብክለትና ተጽዕኖ ቡድን መሪ ወይዘሮ ሰናይት እንደሚገልጹት፣ ድምፅ በመኖሪያ ቤት፣ በምግብ ቤት እና በፋብሪካዎች እንዲሁም ሰው በሚተላለፍባቸው አካባቢዎች ላይ ይለካል። በሚለካበት ወቅት ሰውን በሚረብሽ መልኩ ከሚጠበቀው በላይ ሲሆን የድምፅ ብክለት ተፈጠረ ይባላል። ከዚህ አንጻር የድምፅ ብክለት ማለት ያልተፈለገ ድምፅ ሆኖ በሰዎች የተለመዱ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ በጉዞ፣ በእንቅልፍ፣ በሥራ፣ በትምህርት፣ በንግግር ወይም በመሳሰሉት) ጣልቃ በመግባት የሰው ልጅ ጤናማ ሕይወት ለመምራት የሚያስፈልገውን አካባቢ በመበከል በሥነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ነው። ሆኖም ግን የድምፅ መጠን እንደ ሰሚው ዕድሜ፣ የጤንነት ሁኔታ፣ እንደ ድምፁ ዓይነት፣ ቆይታና ድግግሞሽ የሚለያይ በመሆኑ ለአንዱ መደበኛ ድምፅ ለሌላው የሚረብሽ፤ ለአንዱ የሚረብሽ ድምፅ ለሌላው ሙዚቃ ሊሆን ይችላል።

ኢትዮጵያ የአካባቢ ደህንነት መብትን በሰብአዊ መብት ደረጃ በሕገ መንግሥታቸው ከደነገጉ ጥቂት ሀገራት መካከል ተጠቃሽ ናት። በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 44 (1) ላይ ሁሉም ሰዎች በንጹሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው ተደንግጓል። በአንቀጽ 92 (1) ላይ ደግሞ መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመሥራት ኃላፊነት አለበት። በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ደግሞ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ዜጎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ስለዚህ




**ፎቶ- ከፋይል**
**አዲስ አበባ የድምፅ ብክለትን በቴክኖሎጂ አስደግፉ የመከላከል ስራ እያከናወነች ትገኛለች**

ዜጎች ድምፅን ጨምሮ ከብክለት የጸዳ አካባቢ የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብት አላቸው፤ መንግሥትም ይህን የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል።

ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የአካባቢ ብክለትን የሚመለከት ዝርዝር አዋጅ (የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995) ወጥቷል። አዋጁ ድምፅ ብክለትን በተመለከተ ድንጋጌ ባይኖረውም በአንቀጽ 2 (11) የ"በካይ"ን (Pollutant) ትርጉም ሲያስቀምጥ በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል ድምፅን እንደሚያካትት ያስቀምጣል። በዚህም የድምፅ መጠን ለመወሰን የሚያስችል የአካባቢ ድምፅ ብክለት ክትትልና ቁጥጥር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2014 መመሪያ ወጥቷል። እንደ ቡድን መሪዋ ገለጻ፣ በመመሪያው መሠረት ለመኖሪያ አካባቢዎች በቀን 55፣ በማታ 45 ዲሲቢል መሆን አለበት። ለንግድ አካባቢዎች በቀን 65፣ በማታ 55 ዲሲቢል ሲሆን ለኢንዱስትሪ ዞኖች ደግሞ መውጣት የሚገባው የድምፅ መጠን በቀን 75 በማታ 70 ዲሲቢል መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል።

ቡድን መሪዋ ወይዘሮ ሰናይት የድምፅ ብክለት መንስኤን ሲገልጹ፤ የድምፅ ብክለት በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ሊፈጠር ይችላል። አሽከርካሪዎች ሰው በመስመራቸው ሲገባባቸው አደጋ ላለማድረስ እና ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች ሲጨናነቁ የሚያሰሙት ጡሩንባ የድምፅ ብክለት መፈጠር አንዱ ማሳያ ነው። በአመራረት ሂደት ውስጥም የድምፅ ብክለት ሊፈጠር ይችላል። ለምሳሌ ፋብሪካዎች በምርት ሂደት ወቅት የድምፅ ብቻም ሳይሆን የፍሳሽ ቆሻሻዎችን ወደ አካባቢ በመልቀቅ ተጨማሪ የአካባቢ ብክለት ይፈጥራሉ።

ዋና ዋና ከሚባሉት የድምፅ ብክለት ምንጮች አንዱ የትራንስፖርት ዘርፍ ሲሆን፣ ይህም ከቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ከአውሮፕላን የሚወጣ ድምፅ ነው። ሌላው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለምሳሌ ከብረታ ብረት ፋብሪካዎችና ማቅለጫዎች የሚፈጠረው ነው። የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደ የምሽት ክበባትና ቤተ እምነቶች እንዲሁም ከግንባታ ስፍራዎች የሚወጡ ድምጾች ብክለትን በማድረስ ድርሻቸው ከፍተኛ ነው። የንግድ እና የመኖሪያ ቤቶች እንዲሁም ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚወጣው ድምፅ የብክለት ድርሻው አነስተኛ ቢሆንም ለድምፅ ብክለት መፈጠር ድርሻ አለው።

## የድምፅ ብክለት የሚያስከትለው ተጽዕኖ

የድምፅ ብክለት በሕብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል። የመስማት ችሎታን እስከ መጨረሻው ሊያሳጣ ይችላል። የድምፅ ብክለት በተለይ በአዕምሮ ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና በማሳደር ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በከፍተኛ ሁኔታ ያሳድራል። ትምህርት ቤቶች አካባቢ የድምፅ ብክለት ካለ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ተከታትለው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል። በተመሳሳይ ሆስፒታሎች አካባቢ የድምፅ ብክለት ካለ ሕሙማን ማረፍ ያለባቸውን እረፍት እንዳያገኙና ሕመማቸው እንዲባባስ ያደርጋል። የልብ ችግር ባለባቸው ሰዎች ላይ ደግሞ ችግሩ የባሰ ነው። እንዲሁም አዛውንቶች በሚያርፉባቸው መናፈሻ ስፍራዎች ላይ የድምፅ ብክለት ካለ ስለሚረበሹ የጤና ችግር ሊያስከትልባቸው ይችላል። በተጨማሪም የድምፅ ብክለት ሰዎች ላይ ጭንቀት በመፍጠር በሥራቸው ላይ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል።

## ባለስልጣኑ ችግሩን ለመከላከል ምን እየሰራ ነው?

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የድምፅ ብክለት ችግርን ለመከላከልና ለማስወገድ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ይሠራል። የድምፅ ብክለት ያለባቸውን የተለያዩ ስፍራዎች ቀጥታ ከመለካት ባለፈ ከሕብረተሰቡ የሚመጡ ቅሬታዎችን መሠረት በማድረግ የድምፅ መጠናቸውን በመለካት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። ከጭፈራ ቤት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ቅሬታና በተለዩ ቦታዎች በሚደረገው ልኬት መሠረት ደረጃ ተላልፈው ሲገኙ በቅድሚያ የምክር አገልግሎት ይሰጣል። ከዚህ አለፍ ሲልም ከመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ እስከ ማሸግ፣ የንግድ ፈቃድ መሰረዝና ከቦታው የማስነሳት የደረሱ እርምጃዎች ይወሰድባቸዋል። በበጀት ዓመቱ ባለፉት ስድስት ወራት ከማዕከል እስከ ክፍለ ከተማ ድረስ በሚገኙ 5 ሺህ 780 አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ተሰርቷል። ከእነዚህ ውስጥ ከተፈቀደው መጠን በላይ በመልቀቅ የድምፅ ብክለት ያስከተሉ 1 ሺህ 318 የምሽት ጭፈራ ቤቶች እንዲያስተካክሉ የማስጠንቀቂያ እርምጃ ተወስዷል። 28 የሚሆኑት የምሽት ጭፈራ ቤቶች ደግሞ በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ ባለማድረጋቸው እንዲታሸጉና እንዲዘጉ ተደርገዋል።

## ምን ውጤት እየመጣ ነው?

ቀደም ሲል ሕብረተሰቡ ስለድምፅ ብክለት ጎጂነት ያለው ግንዛቤው አናሳ ነበር። ጎጂነቱን የሚያውቁ ሰዎች እንኳን የት ሄደው ቅሬታ እንደሚያቀርቡ አያውቁም ነበር። በተሰራው ግንዛቤ የመፍጠር እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥራ በአሁኑ ወቅት ሕብረተሰቡ የድምፅ ብክለት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በመገንዘብ በየክፍለ ከተማው በሚገኝ የአካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ቅሬታ ማቅረብ ጀምሯል። ይህም የግንዛቤ እድገቱን የሚያመለክት ነው። አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም በተቀመጠው መስፈርት መሠረት መሥራት ጀምረዋል።

የድምፅ ብክለትን መከላከል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሥራ ብቻ አይደለም። እያንዳንዱ ተቋም እና ግለሰብ በአካባቢው ደህንነት ላይ አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት። ምክንያቱም ለብክለቱ መንስኤ ሕብረተሰቡ ነው። መፍትሄውም ከሕብረተሰቡ መምጣት አለበት። አካባቢ ሳይበከል በንጹሕ አካባቢ ለመኖር የሁሉም ተሳትፎ መኖር አለበት።

በቀጣይም ተከታታይነት ያለው የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ በመሥራት የሕብረተሰቡን፣ የባለሙያውንና የውሳኔ ሰጪውን አካል ግንዛቤና እውቀት የሚያሳድጉ፣ የአመለካከት እና የባህሪ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች በተደራጀና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ማከናወን ያስፈልጋል። በከተማ ፕላን ውስጥ የድምፅ ብክለት ጉዳይን ማካተት፣ እጽዋት በብዛት መትከል፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሻሻልና የአገልግሎት ደረጃ (ስታንዳርድ) እንዲኖራቸው ማድረግ ዋነኛ ተግባር ሊሆን እንደሚገባም ነው የቡድን መሪዋ ያስገነዘቡት።

**መውጣት የሚገባው የድምፅ መጠን ለመኖሪያ አካባቢዎች በቀን 55፣ በማታ 45፣ ለንግድ አካባቢዎች በቀን 65፣ በማታ 55 እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ዞኖች ደግሞ በቀን 75 በማታ 70 ዲሲቢል መሆን አለበት**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የመተባበር የመ/ደ/ት/ቤት በ2018 በጀት ዓመት በሁለተኛ ዙር

- ሎት 1 አላቂ የፅህፈት መሳሪያዎች (የበጀት ርዕስ 6212)-የጨረታ ማስከበሪያ ብር 1,790.50
- ሎት 2 ቋሚ አላቂ የፅህፈት መሳሪያዎች (የበጀት ርዕስ 6219))-የጨረታ ማስከበሪያ ብር1,281.40
- ሎት 3 አላቂ የፅዳት መሳሪዎች (የበጀት ርዕስ 6218))-የጨረታ ማስከበሪያ ብር 2,589.62
- ሎት 4 አላቂ የትምህርት መሳሪያዎች (የበጀት ርዕስ 6215)-የጨረታ ማስከበሪያ ብር113.85
- ሎት 5 የሰራተኞች የደንብ ልብስ እና ስፊት (የበጀት ርዕስ 6211)-የጨረታ ማስከበሪያ ብር 2,345.21
- ሎት 6 ሕትመት (የበጀት ርዕስ 6213)-የጨረታ ማስከበሪያ ብር 1,102.28
- ሎት 7 ለህንጻና፣ ለቁሳቁስ እና ተገጣጣሚዎች መግዥያ (የበጀት ርዕስ 6314) የጨረታ ማስከበሪያ ብር 1,684.43
- ሎት 8 ለህንጻና፣ለቁሳቁስእና ተገጣጣሚዎች እድሳት እና ጥገና (የበጀት ርዕስ 6244) የጨረታ ማስከበሪያ ብር 506.98

በዘርፉ የተሰማሩ አቅራቢዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚሁም መሰረት፡-

1. ተጫራቾች በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ የቲን እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ማስረጃ ማቅረብ የምትችሉ፣ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድህረ ገፅ ላይ በዕቃ አቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ተመላሽ የሚሆን በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (CPO) ከጨረታ ሰነዳችሁ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ አዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት ጀምሮ ለአስር ተከታታይ ቀናት በስራ ሰዓት ት/ቤቱ ግዥ ክፍል በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ አንድ ቀን በፊት ለተወዳደሩባቸው ሎቶች በሙሉ ናሙና ማቅረብ ማዘጋጀትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የምታቀርቡትን ዋጋ ዝርዝር በሰነዱ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ በግልፅ የአንዱን እና ጠቅላላ ዋጋ እስከቫቱ ሞልታችሁ ኦርጅናልና ኮፒ በማለት በታሸገ ኢንቨሎፕ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን 11፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል።
6. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን በ11፡00 ሰዓት ታሽጎ በማግስቱ በ4፡00 በት/ቤቱ ቤተ- መፅሐፍት ይከፈታል። ዕለቱ የበዓል ወይም የእረፍት ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. አሸናፊው ተጫራች ዕቃውን ከማስገባቱ በፊት ከት/ቤቱ ጋር ውል በመፈፀም የውል ማስከበሪያ የዕቃውን 10 ፐርሰንት በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (CPO) ማስያዝ እና ያሸነፏቸውን ዕቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚ መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. የዘገዩ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው እቃ የሚያቀርቡ ድርጅቶች መወዳደር የምትችሉት በምታመርቱት ምርት ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

**አድራሻ፡-** ከአብነት ወደ ሰባተኛ በሚወስደው መንገድ ከብሬን ሆቴል ፊት ለፊት በሚያስገባው አስፋልት ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 03

**ስ.ቁ - 0112 78 85 79**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት**
**መተባበር የመ/ደ/ት/ቤት**

---

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 25 ቀበሌ 03 በአዲሱ አደረጃጀት ወረዳ 11 የሚገኝ ቤት በካርታ ቁጥር (ጂ.አይ.ኤስ)1774/92 በሴሪ ቁጥር 000262 ወ/ት አይናለም ጌታቸው ማሞ ስም የይዞታ/የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት በይዞታ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 መሰረት የባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በ20 (ሃያ ቀን) ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይገኛለው የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 (ሃያ ቀን) ቀን ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በመመሪያው መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትክ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ እንዳለ ገላው ታደሰ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/5/9/7/25203/31045/02 ሴሪ ቁጥር 012579 ተመዝግቦ የነበረው ኦርጂናል/ ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይገኛለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ተገኔ ገ/ሐዋርያት ዘርፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 17 ካርታ ቁጥር ቦሌ (ጂ.አይ.ኤስ) 001584 በሴሪ ቁጥር 003282 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ / የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት / ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይገኛለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በይርጋ ታደሰ ማቲዮስ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/22/10/9/5269/00 የተሰጠበት ቀን 04/01/2004 ዓ.ም የቦታው ስፋት 94 ካ. ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በይርጋ ታደሰ ማቲዮስ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/22/10/9/5269/00 የተሰጠበት ቀን 04/01/2004 ዓ.ም የቦታው ስፋት 94 ካ. ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጂናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይገኛለሁ፣ አስይዤያለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ዋቢ ጥላሁን መርጋ ስም የተመዘገበ ነዋሪነቱ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 መሪ ሎቄ የቤት ቁጥር B-3 ml-B3/hn/705 ካርታ ቁጥር ለ/ኩ/61/1/59586/00 ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረቡ በመሆኑ ካርታ የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይገኛለሁ፣ አስይዤያለሁ የሚል አካል በ20 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ20 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ሀላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ካርታ ቁጥር 6513 በአቶ በላቸው ተከሌ ስም ተመዝግቦ የነበረው ኦርጂናል / ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዜዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለአቶ በላቸው ተከሌ ወራሾች የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሙና አህመዲን መሀመድ ስም በልደታ ክ/ከ በወረዳ 03 በሴሪ ቁጥር L0195564፣ የይዞታ መለያ ቁጥር AA000080301119 ሆኖ የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 11/6/18 ዓ.ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፤ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይገኛለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሣሙኤል ወልደሚካኤል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ካርታ ቁጥር ቦሌ03/290/110-5067/00 በሴሪ ቁጥር 0160473 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይገኛለሁ/ የሚል ይህ ማታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

## የእናቶችና ሕፃናት ዘርፈ ብዙ የልማት ድርጅት (ሜስሚዶ)

### የኦዲት ስራ ጨረታ

### ጨ/ቁ MCMDO 04 /2026

የእናቶችና ሕፃናት ዘርፈ ብዙ የልማት ድርጅት (ሜስሚዶ) በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት ተመዝግቦ በሰርተፍኬት ቁጥር 0022 በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የተለያዩ የልማት ስራዎችን የሚያከናውን ዘርፈ ብዙ የልማት ድርጅት ነው፡፡

ድርጅታችን የእናቶችና ሕፃናት ዘርፈ ብዙ የልማት ድርጅት (ሜስሚዶ) እ.ኤ.አ. የ 2025 በጀት ዓመት የ23 ፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት ማስደረግ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ የኦዲት ድርጅቶች ለሥራዉ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን መስፈርቶቹም፡-

1. የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለዉ
2. በበጀት ዓመቱ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያለዉ
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያለዉ እና በኦዲት ስራ ልምድ ያለዉ
4. ተጫራቾች ከዚህ ቀደም ከሰሩባቸዉ መ/ቤቶች ለሰሩበት የመልካም ስራ አፈፃፀም ማስረጃዎች ማቅረብ የሚችሉ።
5. ግብር የከፈሉ ለመሆናቸዉ ከሀገር ዉስጥ ገቢዎች ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
6. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ እና ስራዉን ሰርተዉ የሚያስረክቡበትን ጊዜ የሚገልፅ ፋይናንሺያል እና ቴክኒካል በተለያዩ በሰም በታሸጉ ኢንቨሎፖች ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል።
7. ጨረታዉ በወጣ በስድስተኛዉ ቀን፣ የስራ ቀን ከሆነ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት ይከፈታል የስራ ቀን ካለሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል።
8. ጨረታዉ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የስራ ቀናት ክፍት ሆኖ ይቆያል።
9. ድርጅቱ ጨረታዉን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቅ ነዉ።

**አድራሻ፡-**

የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የቤት ቁጥር አዲስ ሾላ መብራት በታችኛዉ ከመስጊድ ወደ መገናኛ በሚወስደዉ መንገድ መብራቱን ሳይሻገሩ ከኤጀ ቦሎ ባለዉ መንገድ ፊት ለፊት ያገኙናል።

**ለተጨማሪ መረጃ**

+251112611169 /0979906442

**የእናቶችና ሕፃናት ዘርፈ ብዙ የልማት ድርጅት**

---

አቶ ፀጉ መንገሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100803342 የሴሪ ቁጥር R 033660 በቀን 26/12/2010 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝይቸላው/ይዥዋለው/ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትክ ሌላ ሰርተፍኬት እንሚንሰጣቸው እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 180/75 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN)0003245587 የሚታወቀው በደዊ አብደላ ኤጋቶ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ------- አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 201 እስከ 500 ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- በደዊ አብደላ ኤጋቶ**

---

በርግአት ለገሰ ሐጉስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000081103462220001 በሴሪ ቁጥሩ 152456 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በጀኒ አብርሃም ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 123 የመሬት ይዞታ ካርታ ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000040501989 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን /ዘጠና ቀን/ ድረስ ጽ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ ካልቀረቡ ግን በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቂርቆስ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ሪት ሰለሞን አምበሉ በላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ካርታ ቁጥር AA000060304767040560 ሴሪ ቁጥር 235674 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፊኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ እሸቱ በቀለ ይመኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 011019 ሴሪ ቁጥር 000058 የቦታው ስፋት 94.64 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሰናይት ጠዕመ በላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ ቁጥር AA000080110287220424 ሴሪ 178713 ቁጥር በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ ምስጋናው ከበደ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦ/ስ/10/8/1/8/16040/00 የሴሪ ቁጥር 069650 ወረዳ 10 የቦታው ስፋት 86.04 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና አቶ ምስጋናው ከበደ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦ/ስ/10/8/1/8/16040/00 የሴሪ ቁጥር 069650 ወረዳ 10 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ መሆኑን ያመለከቱ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 13 በተክላይ ሀይሉ ስም የተመዘገበ የኮንዶሚኒየም ቤት የቤቱ ልዩ መለያ ቁጥር AA00005130469122902012 የተሰጠበት ቀን 25/09/2014 ዓ.ም እና ሴሪ ቁጥር C 142612 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/17/42 በቀን 21/09/2017 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የደረሰኝ መጥፋት ማሳወቅ**

በአዲስ አበባ ከተማ የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0087398929 የሚታወቀው ዩ.ኤ.አይ.ት/PLC በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ------------ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የተሰራበት እና ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 1-36 (የተሰራበት) እና ከ37-50 (ያልተሰራበት) ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- ዩኤ አይ ትሬድንግ PLC**

# የቅጥር ማስታወቂያ

**የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።**

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔታ | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የሀብት አስተዳደር ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የንብረት አስተዳደር ባለሙያ | VII | ቢ.ኤ./ ኤም.ኤ ዲግሪ | 4/2 ዓመት | በማናጅመንት፣ማቴሪያል ማኔጅመንት፣ወይም በፕሮክዩሩመንት እና በሳፕላይስ ማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.913 እና አ/18.914 | 2 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን የካቲት 23 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ የመጋቢት 04 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

## አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በአቶ ብርሃኑ ወዳጆ ገሰሰ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 06 ቤ/ቁጥር 238/25 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000061000300238O425 የይዞታ ማረጋገጫ የምስክረ ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 (ሰላሳ) ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ፤ ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ/6147/12 ሴሪ ቁጥር 1500345 በወ/ሮ ፀሀይ አሰፋ አርዶፋ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ሙሉቀን አያሌው አሰፋ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ለሚ ኩራ 09/34/1/42998/0501/1/00 የሴሪ ቁጥር 1668350 ወረዳ 9 የቦታው ስፋት 162.52 ካ.ሜ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና አቶ ሙሉቀን አያሌው አሰፋ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር 09/34/1/42998/0501/1/00 የሴሪ ቁጥር 1668350 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ መሆኑን ያመለከቱ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያለን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በመስፍን ውቤ አየለ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ9/36/2/45599/0089/12/00 የተሰጠበት ቀን 25/02/2015 ዓ.ም የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በመስፍን ውቤ አየለ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ9/36/2/45599/0089/12/00 የተሰጠበት ቀን 25/02/2015 ዓ.ም የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ፍሬዘውድ ሰቦቃ ዳቢ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061400745001O3007 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በፀጋዬ ተወልደ አፅብሃ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር 01/52/10991/62992/01 በሴሪ ቁጥሩ 031490 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ፀጋዬ ተወልደ አፅብሃ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ ቁጥር AA000080105983 ሴሪ ቁጥር 0139445 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ፋኑኤል አብርሃም ሰለሞን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ልዩ መለያ ኮዱ AA000060104557 የሆነው ይዞታ እና በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቻዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 064 በእነ መዲሐኒት ተስፋዬ ገብረፃዲቅ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) ወ12/ውዝ01/457/12002/01 ሴሪ ቁጥር 062257 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 18/06/2018 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# በሮም የተደገመው የዓድዋ ድል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

‘አይቻልም’ የሚለው ቃል በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያለ ተራ ቃል ብቻ ሳይሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ሰዎችና ሁኔታዎች በፊታችን ላይ የሚደቅኑት ግድግዳም ጭምር ሆኖ እናገኘዋለን። ይሁንና በታሪክ ውስጥ ይህንን ግድግዳ አምርረው ከናቁ ክስተቶች መካከል ሁለቱ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። አንደኛው ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት በዓድዋ ተራሮች ላይ በጀግኖች ኢትዮጵያውያን የተጻፈ የነፃነት ታሪክ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከስልሳ ዓመታት በኋላ በሮም አውራ ጎዳናዎች ላይ በጀግናው አትሌት አበበ ቢቂላ የተሠራው የጽናት ተአምር ነው።

ለአንድ አፍታ በምናብ ወደ ኋላ ወደ አስገራሚው የሮም ድል መለስ ብንል የምናየው ስሜት፣ ዓድዋ ላይ የነበረው ያ የማይበገር የነፃነት ወኔ በ1952 ዓ.ም በሻምበል አበበ ቢቂላ ልብ ውስጥ ዳግም ሲቀጣጠል ነው። አበበ በሮም አስፋልት ላይ በባዶ እግሩ ሲሮጥ፣ የሚረግጠው ድንጋዩንና ትኩሱን አስፋልት ብቻ አልነበረም፤ ‘ጥቁር ሕዝብ አይችልም’ የሚለውን የዓለምን የተሳሳተ አመለካከት ጭምር እንጂ።

የሮም ኦሎምፒክ ማራቶን ሊጀመር ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ፣ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞችና ታዛቢዎች በአንድ ነገር ግራ ተጋብተው ነበር። አንድ ቀጭን ኢትዮጵያዊ ሯጭ፣ በዘመናዊው ስፖርት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ያለምንም ጫማ በመነሻ መስመር ላይ ቆሟል። ያኔ ብዙዎች አበበ ቢቂላን እንደ አንድ ተራ ሯጭ ብቻ ሳይሆን፣ ጫማ የሌለው ምስኪን አፍሪካዊ አድርገው ነበር የቆጠሩት።

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ተራሮች ላይ ዓለምን ያስገረመ ታሪክ ሲሠሩ፣ ለአፍሪካውያንና ለመላው ጥቁር ሕዝቦች “የማይቻል የለም” የሚል የድል ብርሃን ፈንጥቀው ነበር። ይህ የዓድዋ መንፈስ፣ ከ64 ዓመታት በኋላ በ1952 ዓ.ም በሌላ መልኩ በሮም አውራ ጎዳናዎች ላይ ዳግም ታየ። ይህ ክስተት የዓድዋ ድል በጦር መሣሪያ የተመዘገበ እንደሆነው ሁሉ፣ የሮም ድል ደግሞ ‘በላብና በጽናት’ የተመዘገበ ሁለተኛው የዓድዋ ድል ነበር። አበበ ቢቂላ ጫማ ባለመጫማቱ አልተሸማቀቀም፤ ይልቁንም “እግሬን የሚያቆስለኝ ጫማ እንጂ አስፋልቱ አይደለም” በሚል ኩራት፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በድል አደባባይ ላይ ከፍ አደረገ።

አበበ ቢቂላ ወደ ሮም ኦሎምፒክ ሲያቀና፣ አዳዲስ የሩጫ ጫማዎች እግሩን ስላቆሰሉት አንድ ከባድ ውሳኔ ወሰነ፤ በባዶ እግር መሮጥ፡፡ አስፋልቱ ይሞቃል፤ ድንጋዮቹ ይወጋሉ፤ ርቀቱ 42 ኪሎ ሜትር ነው። የሮምን አውራ ጎዳናዎች በባዶ እግሩ እየቀደደ፣ የፋሽስት ሞሶሊኒ ጦር ኢትዮጵያን ለመውረር የተነሳበትን የአክሱም ሐውልት አጠገብ አልፎ በመጀመሪያነት ሲገባ ዓለምን ያስገረመ ታሪክ ተሠራ።

የዓድዋ ድል ለመላው የጥቁር ሕዝቦች የድል ማሳያ እንደሆነ ሁሉ፣ የአትሌት አበበ ቢቂላ ድልም ለጥቁር አፍሪካውያን የመጀመሪያውን የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ በማምጣት በስፖርቱ ዓለም አዲስ ምዕራፍ ከፈተ። ዓድዋ ላይ ዘመናዊ መሣሪያ ሳይኖር በሀገር ፍቅር እንደተሸነፈ ሁሉ፣ አበበም ውድ ጫማ ሳይኖረው በጽናት አሸነፈ። በወቅቱ አትሌት አበበ ቢቂላ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጠው አስተያየት “ሁልጊዜም የምሮጠው ለድል ነው። ኢትዮጵያ ሁልጊዜም በጽናትና በድል አድራጊነት እንደምትኖር ለዓለም ማሳየት እፈልጋለሁ” ነበር ያለው፡፡

ታዋቂው የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት፣ የአበበን ድል ከአክሱም ሐውልት መመለስ ጥያቄ ጋር አያይዘውት ነበር። ፓንክረስት፣ ድሉ ለኢትዮጵያውያን የሰጠውን የሞራል ልዕልና ሲገልጹ፣ “አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ መሮጡ፣ ኢትዮጵያ ካሏት ሀብቶች ይልቅ በውስጣዊ ወኔና በሰው ኃይል ማንኛውንም ተግዳሮት ማሸነፍ እንደምትችል ለዓለም ያስመሰከረበት ክስተት ነበር” ብለዋል።

ብዙዎቹ አፍሪካውያን ምሁራን አበበን “የፓን-አፍሪካኒዝም አምባሳደር” ይሉታል። እ.ኤ.አ 1960 “የአፍሪካ ዓመት” ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፣ በዚያው ዓመት አበበ የመጀመሪያውን ወርቅ ለአፍሪካ ማምጣቱ የተለያዩ ትርጉሞችን አስጥቷል። በወቅቱ አውሮፓውያን “ጥቁር ሕዝብ ለረጅም ርቀት ሩጫ ብቃት የለውም” የሚለውን ሳይንሳዊ ግምት አበበ ውድቅ ማድረጉን ምሁራን በስፋት ጽፈውበታል። በሌላም በኩል ዓድዋ የጥቁር ሕዝብ የፖለቲካ ነፃነት ምልክት እንደሆነው ሁሉ፣ አበበ ቢቂላ ደግሞ የጥቁር ሕዝብ የአካልና የሥነ-ልቦና ብቃት ምልክት መሆኑን ያስምሩበታል።

በዓድዋ ድል እና በአበበ ቢቂላ የሮም ድል መካከል ያለውን ተምሳሌታዊ ትስስር፣ የታሪክ አንድነት እና የስነ-ልቦና ጥንካሬ የመረመሩ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች አሉ። “Abebe Bikila: The Barefoot Runner and the Spirit of Adwa” የተሰኘው ጥናታዊ ጽሑፍ አበበ ቢቂላን እንደ “ሁለተኛው የዓድዋ ጀግና” ይስለዋል። ጥናቱ አበበ በሮም ኦሎምፒክ ያሸነፈው ሩጫ “የተገዥዎች በቀል” (Revenge of the Colonized) ተብሎ ሊጠራ እንደሚችል ይተነትናል። ጣሊያን ዓድዋ ላይ በጦር መሣሪያ የተሸነፈችውን ሽንፈት በሥልጣኔ ስም ልታክም በሞከረችበት መድረክ፣ አበበ በባዶ እግሩ መጥቶ ማሸነፉ የዓድዋን ድል በዲፕሎማሲና በስፖርት መድረክ ያደሰ ክስተት ስለመሆኑም በጥናቱ ላይ ሰፍሯል።

“Barefoot Runner: The Life of Marathon Champion Abebe Bikila” የተሰኘው መጽሐፍ ደራሲ እንግሊዛዊው ፖል ራምቦል በበኩላቸው፣ አበበን የሚስሉት እንደ ተራ አትሌት ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና ኩራት መገለጫ አድርገው ነው።

አበበ ቢቂላ በሮም አውራ ጎዳናዎች ላይ በባዶ እግሩ ሲሮጥ፣ የተሸከመው የራሱን ሕልም ብቻ አልነበረም የሚሉት ፖል ራምቦል ይልቁንም ለዘመናት ሳይበገሩ የቆዩትን የአባቶቹን ጽናትና የዓድዋን የድል መንፈስ ጭምር ነው ይላሉ። አያይዘውም፣ ለእርሱ ሮም የውድድር ስፍራ ብቻ ሳትሆን፣ ኢትዮጵያውያን ለማንነታቸውና ለነፃነታቸው የሚከፍሉትን መሥዋዕትነት በስፖርታዊ ጨዋነት ለዓለም ዳግም የምታሳይበት መድረክ ነበረች። በዚያች ታሪካዊ ምሽት አበበ ያሸነፈው ሩጫውን ብቻ ሳይሆን፣ ‘ጥቁር ሕዝብ አይችልም’ የሚለውን የዓለምን ጥርጣሬ በደከመውና በቆሰለው እግሩ ረግጦ በማለፍ ጭምር ነበር ብለዋል፡፡

የዓድዋ ድል እና የአበበ ቢቂላ የሮም ድል ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካውያን ‘የነፃነት’ እና ‘የችሎታ’ መገለጫ ተደርገውም ይወሰዳሉ። የዓድዋ ድል አውሮፓውያን አፍሪካን የመገዛት ዕጣ ፈንታ ያላት አድርገው ይስሏት የነበረውን ትረካ ሰባብሯል። ይህ ድል ለበርካታ የአፍሪካ ሀገራት የነፃነት ታጋዮች እንደ ብርሃን ሆኖ አገልግሏል። ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ነፃ ሲወጡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ቀለሞች (አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ) ለባንዲራቸው መምረጣቸው የዓድዋ ድል ያስገኘው ተጨባጭ የፓን-አፍሪካኒዝም ማስረጃ ተደርጎም ሊወሰድ የሚችል ነው።

ከአበበ ድል በፊት፣ ረጅም ርቀት ሩጫ ለአውሮፓውያንና ለአሜሪካውያን ብቻ የተተወ ይመስል ነበር። የአበበ ድል በመላው አፍሪካ (በተለይ በምስራቅ አፍሪካ እንደ ኬንያ እና ታንዛኒያ) ለሚገኙ አትሌቶች መንገድ ከፋች ሆኗል። ዛሬ ዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድሮች በአፍሪካውያን ቁጥጥር ስር መውደቃቸው፣ መነሻው የዓድዋ መንፈስ የወለደው የአበበ ቢቂላ ‘የይቻላል’ ጽናት ስለመሆኑም እሙን ነው።

አበበ ቢቂላ በሮም ኦሎምፒክ ሲያሸንፍ 17 የአፍሪካ ሀገራት ነፃነታቸውን ያገኙበት “የአፍሪካ ዓመት” ነበር። ዓድዋ አፍሪካውያን በጦር ሜዳ “እንችላለን” እንዲሉ እንዳደረጋቸው ሁሉ፣ አበበ ደግሞ ሰላማዊ በሆነው የዓለም ስፖርት መድረክ አፍሪካውያን ከነጭ ዘር እኩል አልፎም የተሻለ ብቃት እንዳላቸው በተግባር አሳይቷል።

የዓድዋ ድል የነፃነታችን መሠረት እንደሆነው ሁሉ፣ የአበበ ቢቂላ የሮም ድልም የኢትዮጵያውያን የጽናትና የ“ይቻላል” መንፈስ ማሳያ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል። ዛሬም እንደ ሀገር የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ለማለፍ፣ ያንን ጥንካሬና የማይበገር ማንነት ዳግም ማንቃት ይጠበቅብናል። እንደዚሁም ዛሬ ስለ ዓድዋ ሲወራ ስለ ጦርነት ብቻ አይደለም የሚወራው፤ ዛሬ ስለ አበበ ቢቂላም ሲወራ ስለ ሩጫ ብቻ አይደለም የሚወራው። ይልቁንስ ዛሬ ላይ የሚወራው ማንኛውንም ተግዳሮት “ይቻላል” ብሎ ስለሚጋፈጠው ያ ኢትዮጵያዊ የጥንካሬ መንፈስ እንጂ።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1960 በሮም ኦሎምፒክ በባዶ እግሩ ሮጦ ዓለምን ያስደመመው ሻምበል አበበ ቢቂላ